
# አማርኛ

## እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ



### ሶስተኛ ክፍል

በአዲስ አበባ ት/ቢሮ ተዘጋጅቶ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ትምህርት ቢሮ እና በዲላ መምህራን ት/ኮሌጅ የተስማማ

የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ

# አማርኛ ቋንቋ

# (እንደ አፍ መፍቻ)

# የተማሪ መጽሐፍ

## ሦስተኛ ክፍል

የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ

# አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ

# የተማሪ መጽሐፍ

# ሶስተኛ ክፍል

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር በአዲስ አበባ ከተማ ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ፣
በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ እና በዲላ ትምህርት ኮሌጅ ተስማምቶ የተዘጋጀ


አስማማቶ አዘጋጆች፦

ትእግስት ዳዊት

ማርቆስ በላቸው

መኮንን ሆርዶፋ

አርታኢ፦

እንግዳወርቅ እንድርያስ



የደቡብ ክልል ትምህርት ቢሮ

ጥቅምት 2014

# ማውጫ

ምዕራፍ አንድ ........ 1
**ጤና ........ 1**
ምዕራፍ ሁለት ........ 14
**ጉርብትና ........ 14**
ምዕራፍ ሶስት ........ 26
**ተረት ........ 26**
ምዕራፍ አራት ........ 37
**የጊዜ አጠቃቀም ........ 37**
ምዕራፍ አምስት ........ 46
**መዳዳዣ ........ 46**
ምዕራፍ ስድስት ........ 59
**ስነ ምግባር ........ 59**
ምእራፍ ሰባት ........ 69
**ግብርና ........ 69**
ምእራፍ ስምንት ........ 82
**ስራ ........ 82**
ምእራፍ ዘጠኝ ........ 96
**ባህል ........ 96**
ምዕራፍ አስር ........ 107
**ገበያ ........ 107**
የቃላት ፍች ........ 119
ዋቢ ፅሁፎች ........ 121

# መግቢያ

ይህ የመማሪያ መጽሐፍ አማርኛን እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀ ነው፡፡ መጽሐፉ አስር ምዕራፎች አሉት፡፡ በየምዕራፎቹ ውስጥ የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች በተጨማሪም የቃላትና የሰዋስው ይዘቶች ከትረካ ጋር ቀርበዋል፡፡ ለትምህርት የቀረቡት ክሂሎችና ይዘቶች በምሳሌ ተደግፈው የቀረቡ በመሆናቸው ተማሪዎቹን በተግባር እንዲሳተፉ የሚያግዙ ናቸው፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## ጤና

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- **ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ዘገባ በቃል ታቀርባላችሁ፡፡**
- **የተሰጣችሁን ምንባብ በትክክለኛው አገላለጽ ታነባላችሁ፡፡**
- **ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ትርጉም ትሰጣላችሁ፡፡**
- **የአረፍተ ነገር አያያዦችን ለይታችሁ ትጠቀማላችሁ፡፡**

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

### የጥርስ ንጽህና አጠባበቅ



### የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ከስዕሉ ምን ተረዳችሁ?
2. የጥርስ ንጽህና አጠባበቅ ምንድን ነው?
3. አንድ ሰው በቀን ቢያንስ ስንት ጊዜ ጥርሱን መቦረሽ አለበት?

## ተግባር አንድ፡ አዳምጦ መረዳት

**ሀ. ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

1. ቀደም ሲል ባዳመጣችሁት ምንባብ ውስጥ የተጠቀሱት ስሞች ማንና ማን ናቸው?
2. ተማሪዎች የሚኖሩበት ከተማ የት ነው?
3. ተማሪዎቹ ስንተኛ ክፍል ናቸው?
4. ያዳመጣችሁት ምንባብ ማስተላለፍ የፈለገው መልዕክት ምንድን ነው?

**ለ.ከላይ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ሀሳባችሁን በጽሁፍ ግለጹ፡፡**

1. የጽሁፉ ዋና ሃሳብ ምንድን ነው?
2. ጫኪሶ የጥርስ ንጽህናውን ከመጠበቅ አኳያ ማድረግ የነበረበትን ተግባራት በጽሁፍ ግለጹ፡፡

## ተግባር ሁለት፡-ቃላት

**ሀ. ከዚህ በታች ለተሰጡት ቃላት ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ተመሳሳይ ፍቻቸውን ፃፉ፡፡**

**ምሳሌ፡-** ሄደ = ተጓዘ

| | |
|---|---|
| 1.ቦረሸ | 2. በተደጋጋሚ |
| 3. በፀና | 4. ጓደኛ |
| 5. ወላጅ | |

ለ. ከዚህ በታች ለተሰጡት ቃላት ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ተቃራኒ ፍቻቸውን ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- ሄደ = መጣ

1. ጎበዝ
2. ታመመ
3. ንፁህ
4. ጠዋት
5. ሴት

## ተግባር ሶስት፡- መፃፍ

**ምሳሌውን መሰረት በማድረግ በሚከተሉት ቃላት አረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡**

**ምሳሌ**፡- 1. ጓደኛ

2. ተማሪ

1. መሀመድ የሀና ጓደኛ ነው፡፡
2. ዘምዘም ጎበዝ ተማሪ ናት፡፡

**ከላይ በቀረቡት ምሳሌዎች ጓደኛና ተማሪ በሚሉት ቃላት ሁለት አረፍተ ነገሮችን መመስረት ተችሏል፡፡ ተማሪዎች እናንተም ከዚህ በታች በቀረቡት ቃላት አረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡**

1. ቀን
2. ሰው
3. ክፍል
4. ጥርስ
5. ጤና ጣቢያ
6. ሀኪም
7. መከረ

## ክፍል ሁለት፡- ንባብ

### የአካባቢና የግል ንጽህና



### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች፡-

1. ስዕሉን በመመልከት የተገነዘባችሁትን ሀሳብ በቃል ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለፁ፡፡
2. ከርዕሱ ተነስታችሁ ምንባቡ ስለምን የሚያስረዳ ይመስላችኋል?

### አካባቢና የግል ንፅህና

ጤናማ ለመሆን የአካባቢንና የግል ንፅህናን መጠበቅ አስፈላጊ ነው፡፡ ሰዎች እንዳይታመሙ አስቀድመው ጥንቃቄ ለማድረግ አካባቢያቸውንና የግል ንፅህናቸውን በሚገባ መጠበቅ ይኖርባቸዋል፡፡

የአካባቢን ንፅህና ለመጠበቅ የአካባቢው ማህበረሰብ አካባቢውን በጋራ ማፅዳት ይጠበቅበታል። በዚህም ከተለያዩ ተላላፊ በሽታዎች ማለትም እንደ ጉንፋን፣ ወባ ከመሳሰሉት ሊጠበቁ ይችላሉ።

**ሰዎች የአካባቢያቸውንና የግል ንፅህናቸውን ባይጠብቁ ምን የሚሆኑ ይመስላችኋል?**

በአንድ በኩል እያንዳንዱ ሰው የግል ንጽህናውን በመጠበቅ ጤንነቱን መጠበቅ ይችላል። የግል ንፅህና ሲባል ልብስን በአግባቡ ማጠብ፤ ጸጉርን አጥቦ ማበጠር፤ እጅን በሳሙና በደንብ መታጠብ፤ እግርን መታጠብ፤ የካልሲና የጫማ ንጽህና መጠበቅ ያስፈልጋል። በሌላ በኩል ሰዎች በአካባቢና በግል ንጽህና ጉድለት ሲታመሙ ፈጥነው ወደ ሀኪም ቤት መሄድ አለባቸው። ሀኪም ቤት ሄደው በሽታቸው ከተገኘ በኋላ የሚሰጣቸውን መድሀኒት በአግባቡ መውሰድ ይኖርባቸዋል። በአጠቃላይ ሰዎች የአካባቢንና የግል ንፅህናን መጠበቅና ሲታመሙ መታከም በጤና ለመኖር ያስችላቸዋል።

**ተግባር አንድ:- አንብቦ መረዳት**

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃል መልሱ።**

1. ጤናማ ለመሆን ምን ማድረግ ያስፈልጋል?
2. ሰዎች ወደ ሀኪም ቤት የሚሄዱት ለምንድን ነው?
3. አንድ ሰው ሲታመም ምን ማድረግ አለበት ትላላችሁ?
4. የአካባቢውንና የግል ንፅህናውን የማይጠብቅ ሰው ምን ሊገጥመው ይችላል?
5. አንድ ሰው ሀኪም ቤት የሚሰጠውን መድሀኒት በአግባቡ መውሰድ ያለበት ለምንድን ነው?

**ለ. ከዚህ በታች ለቀረቡ ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ በፅሁፍ ሀሳባችሁን አስፍሩ፡፡**

1. የምንባቡን ዋና ሀሳብ በሶስት አረፍተ ነገሮች ግለፁ፡፡
2. የግልና የአካባቢን ንፅህና አንድነትና ልዩነት በፁሁፍ አብራሩ፡፡
3. የግል ንፅህናችንን በሚገባ እየጠበቅን የአካባቢያችንን ንፅህና ባንጠብቅ ምን የሚከሰት ይመስላችኋል?

**ሐ. በሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ክፍት ቦታዎች ከሰንጠረዡ ውስጥ ተስማሚ ቃላትን በመምረጥ አሟልታችሁ ፃፉ፡፡**

| | | |
|---|---|---|
| ሀኪም ቤት | ሰዎች | የአካባቢውን ንፅህና |
| መድሀኒት | የግል ንፅህና | በጤና |

1. ----------------ለመኖር የአካባቢንና የግል ንፅህናን መጠበቅ ይኖርብናል፡፡
2. ሰዎች ከሃኪም ቤት የሚሰጣቸውን-------------------በአግባቡ መውሰድ አለባቸው፡፡
3. -----------------እንዳይታመሙ አስቀድመው የአካባቢያቸውንና የግል ንፅህናቸውን መጠበቅ አለባቸው፡፡
4. እያንዳንዱ ሰው የራሱን ------------------መጠበቅ አለበት፡፡
5. ኅብረተሰቡ በጋራ በመሆን ----------------------መጠበቅ ይችላል፡፡

**ተግባር ሁለት፡- አቀላጥፎ ማንበብ**

ተማሪዎች ገጽ 4 እና 5 ላይ ‹‹የአካባቢና የግል ንጽህና›› በሚል የቀረበውን ምንባብ እንደገና ተራ በተራ ድምጻችሁን ከፍ አድርጋችሁ ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

## ክፍል ሶስት፡- ቃላት

### ተግባር አንድ ፡- የቃላት ፍቺ

**ሀ. በ "ሀ" ስር ለተዘረዘሩት ቃላት በ "ለ" ስር ተመሳሳይ ፍቻቸውን በመምረጥ አዛምዱ፡፡**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. መጠቃት | ሀ. በአስቸኳይ |
| 2. ተላላፊ | ለ. መጋለጥ |
| 3. በፍጥነት | ሐ. ተዛማጅ |
| 4. ሀኪም ቤት | መ. ማፅዳት |
| 5. ማጠብ | ሠ. የህክምና ተቋም |

**ለ. በ "ሀ" ስር ለተዘረዘሩት ከ "ለ" ተቃራኒያቸውን በመምረጥ አዛምዱ**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ማኅበረሰብ | ሀ. በተናጠል |
| 2. በጋራ | ለ. ቆሻሻ |
| 3. በሽተኛ | ሐ. ግለሰብ |
| 4. ንፁህ | መ. በኋላ |
| 5. በቅድሚያ | ሠ. ጤነኛ |

**ሐ. ከዚህ በታች በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ያላቸውን አውዳዊ ፍች በፅሁፍ መልሱ፡፡**

**ምሳሌ፡-** ሀ. በአካባቢና በግል ንፅህና ጉድለት ምክንያት ሲታመሙ <u>ፈጥነው</u> ወደ ሀኪም ቤት መሄድ አለባቸው፡፡

**መልስ፡-** <u>ፈጥነው</u> የሚለው ቃል በአረፍተ ነገሩ ውስጥ ያለው አውዳዊ ፍች <u>ቶሎ</u> የሚል ይሆናል፡፡

ለ. ጥንቃቄ በማድረግ <u>በሽታን</u> መከላከል ይቻላል፡፡

**መልስ፡-** <u>መከላከል</u> የሚለው ቃል በአረፍተ ነገሩ ውስጥ ያለው አውዳዊ ፍች <u>መቆጣጠር</u> የሚል ይሆናል፡፡

1. ህጻናት የተመጣጠነ ምግብ <u>መመገብ</u> አለባቸው፡፡
2. በወባ በሽታ <u>የተያዘ</u> ሰው ያንቀጠቅጠዋል፡፡
3. ወይዘሮ ንግስት ህመሟ <u>ጠናባት</u>፡፡
4. ካሊድ ጠዋት ጠዋት <u>ሁል ጊዜ</u> ጸጉሩን ይታጠባል፡፡
5. ሂክማ ለቤት ቁሳቁስ መግዣ <u>ገንዘብ</u> ወጪ አደረገች፡፡

**መ. ከዚህ በታች በቀረበው ሰንጠረዥ ውስጥ ያሉትን ቃላት ባለሶስት ወይም ባለ አራት ሆሄ መሆናቸውን የራይት ምልክት በመጠቀም አመልክቱ፡፡**

| ተ.ቁ | የተሰጡ ቃላት | ባለሶስት ሆሄ ቃላት | ባለአራት ሆሄ ቃላት |
|---|---|---|---|
| 1 | ለበሰ | ✓ | |
| 2 | ሰበሰበ | | ✓ |
| 3 | ከበረ | | |
| 4 | ደብተር | | |
| 5 | እርሳስ | | |
| 6 | ተማሪ | | |
| 7 | ጠረጴዛ | | |
| 8 | አጠበቀ | | |

**ሠ. በምሳሌው መሰረት ከዚህ በታች የቀረቡትን ቃላት ነጠላ ወይም ብዙ ቁጥር በማለት ለይታችሁ ፃፉ፡፡**

ምሰሌ፡- ደብተር- ነጠላ ቁጥር

ተማሪዎች፡- ብዙ ቁጥር

1. ቤት
2. ድመቶች
3. ሴቶች
4. ደግ
5. መኪና
6. ቴሌቪዥን
7. ብርቱካኖች
8. ወንበር
9. እናቶች
10. መምህር

## ክፍል አራት፡- ፅህፈት

### ተግባር አንድ፡- መፃፍ

**ሀ. ከዚህ በታች ተዘበራርቀው የቀረቡትን የድርጊት ቅደም ተከተሎች እንደገና አስተካክላችሁ ፃፉ፡፡**

1. ወደ መጸዳጃ ቤት ሄዱ፡፡
2. የደንብ ልብሳቸውን ለበሱ፡፡
3. እጃቸውንና ፊታቸውን ታጠቡ፡፡
4. ደብተራቸውን፣መፅሀፋቸውን፣እርሳስና እስክሪብቷቸውን ወደ ቦርሳቸው ከተቱ፡፡
5. ወደ ትምህርት ቤት ሄዱ፡፡
6. ከእንቅልፋቸው ተነሱ፡፡
7. ቦርሳቸውን ያዙ፡፡

**ለ. የሳይንስ መምህራችሁን ወይም የጤና ባለሙያ ስለ ኮረና ቫይረስ መተላለፊያና መከላከያ መንገዶች ጠይቃችሁ በቡድን ፅፋችሁ ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡**

**ሐ. የአካባቢና የግል ንፅህና አጠባበቅ አስመልክቶ ከቤተሰቦቻችሁ ወይም ከጎረቤቶቻችሁ በግል ጠይቃችሁ ፅፋችሁ በመምጣት ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡**

## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

## ተግባር አንድ አያያዥች

**ማስታወሻ**

አያያዦች ቃልን ከቃል፣ ሀረግን ከሀረግና አረፍተ ነገርን ከአረፍተ ነገር ጋር የሚያያይዙ ናቸው፡፡ አያያዥ ቃላት ወይም ሐረጋት ከሚባሉት መካከል **ለምሳሌ**

ነገር ግን፣እንጂ፣እና፣ ስለዚህ ወዘተ. ተጠቃሽ ናቸው፡፡

**ሀ. ከዚህ በታች በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን አያያዥ ቃላት ወይም ሀረጋት ምሳሌውን መሰረት በማድረግ በቡድን ሆናችሁ አስምሩባቸው፡፡**

**ምሳሌ፡-**ሀ.ትምህርት ቤት መሄድ እፈልጋለሁ <u>ነገር ግን</u> ደክሞኛል፡፡

ለ. ያሬድ ጎበዝ ተማሪ <u>ስለሆነ</u> ጥሩ ውጤት አስመዘገበ፡፡

1. የሰፈራችን ልጆች መልካሞች ስለሆኑ የተቸገረ ይረዳሉ፡፡
2. ኢትዮጵያ የጀግኖች ሀገር እንጂ የሌቦች አይደለችም፡፡
3. ሰአዳ መምህር እንጂ ሀኪም አይደለችም፡፡
4. ፈተና ደርሷል ስለዚህ ማንበብ አለብን፡፡
5. ይሳኮር መፅሃፍ ማንበብ ሲወድ ቅድስት ግን ፊልም ማየት ትወዳለች፡፡

6. አዲስ አበባ የቱሪስት መዳረሻ ብትሆንም በቂ የመዝናኛ ቦታዎች የሏትም፡፡

**ለ. ከዚህ በታች በቀረቡት አያያዥ ቃላት በመጠቀም በምሳሌው መሰረት አረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡**

**ምሳሌ፡-** ነገር ግን

ደመናው ዳምኗል <u>ነገር ግን</u> ዝናብ አይጥልም፡፡

1. ስለሆነም
2. ስለዚህ
3. ይሁን እንጂ
4. ነገር ግን
5. ቢሆንም
6. እና

## የክለሳ ጥያቄዎች፡-

1. የግልና የአካባቢ ንፅህና አጠባበቅ አስመልክቶ በሬድዮና በቴሌቭዥን የሚተላለፉ መረጃዎችን አዳምጣችሁ በመምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ፡፡
2. የግልና የአካባቢ ንፅህና አጠባበቅ አስመልክቶ የተፃፉ ምንባቦችን ፈልጋችሁ በማምጣት በክፍል ውስጥ አቀላጥፋችሁ አንብቡ፡፡
3. ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍች ስጡ፡፡

ሀ. ተጋላጭ                    መ. መዛባት

ለ. በጥሞና                    ሠ. መጠበቅ

ሐ. በትጋት                                ረ. ፈጠራ

4. በግልና አካባቢ ንፅህና አጠባበቅ ጉድለት ሊከሰቱ የሚችሉ የጤና እክሎችን በአምስት አረፍተ ነገሮች ፃፉ፡፡

5. በሚከተሉት አያያዥ ቃላትና ሀረጋት አረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡

ሀ. ስለሆነም

ለ. እንጂ

ሐ. ነገር ግን

መ. ቢሆንም

ሠ. ስለዚህ

# ምዕራፍ ሁለት

## ጉርብትና

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- የምንባቡን ታሪክ አዳምጣችሁ በድጋሚ ትናገራላችሁ፡፡
- አጫጭር ምንባቦችን አቀላጥፋችሁ ታነባላችሁ፡፡
- ለቃላት ተቃራኒና ተመሳሳይ ፍች ትሰጣላችሁ፡፡
- ስርአተ ነጥቦችን ተጠቅማችሁ አረፍተ ነገር ትጽፋላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር



ጉርብትና እና ጠቀሜታው

## የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች፦

1. ስዕሉን ተመልክታችሁ የተገነዘባችሁትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ፡፡
2. ርዕሱን ተመልክታችሁ ስለምን እንደሚገልፅ ተናገሩ፡፡
3. መልካም ጉርብትና ማለት ምን ማለት ነው?

## ተግባር አንድ፦ አዳምጦ መረዳት

**ሀ. ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

1/ ባዳመጣችሁት ምንባብ ውስጥ በመልካም ጉርብትናቸው የተጠቀሱት እነማን ናቸው?

2/ የተጣላን የሚያስታርቁትና የተቸገረን የሚረዱት እነ ማን ናቸው?

3/ አቶ አምሀ ሴት ልጃቸውን ሲድሩ ጎረቤቶቻቸው ምን አደረጉላቸው?

4/ ወይዘሮ ሀያትና አቶ አምሀ በጎረቤቶቻቸው ደስተኛ የሆኑት ለምንድን ነው?

5/ የሰርግ ስነሰርዓቱን ከስራ ጀምሮ እስከ ፍጻሜው ያደመቁት እነ ማን ናቸው?

6/ የሰው ልጆች መልካም ጎረቤት ባይኖራቸው ምን ይሆናሉ?

**ለ. ከዚህ በታች የቀረቡትን አረፍተ ነገሮች አንብባችሁ የያዙት ሀሳብ ትክክል ከሆነ እውነት ስህተት ከሆነ ደግሞ ሀሰት በማለት በቃል መልሱ፡፡ ምክንያታችሁንም ግለፁ፡፡**

1. የመልካም ጉርብትና መኖር የሰዎችን ማህበራዊ ህይወት ያጠናክራል፡፡
2. በቤታቸው እንግዳ ተቀባይ ናቸው የተባሉት ወይዘሮ ሀያት ናቸው፡፡

3. ከዩኒቨርሲቲ ተመርቆ የመጣው የአቶ አምሀ ሁለተኛ ልጅ ነው፡፡
4. አቶ አምሀና ወይዘሮ ሀያት የሚኖሩት ጤና ጣቢያ አካባቢ ነው፡፡
5. በመልካም ጉርብትና የሚኖሩ ሰዎች እርስ በእርስ መደጋገፍ አለባቸው፡፡

**ሐ. ከዚህ በታች በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ጥንድ ጥንድ በመሆን ተነጋግራችሁ የደረሳችሁበትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በጽሁፍ አቅርቡ፡፡**

1. እናንተ በአካባቢያችሁ የምታውቁዋቸውን ጎረቤቶቻችሁን ስሞች ጥቀሱ፡፡
2. ከጎረቤቶቻችሁ ጋር ስትኖሩ ለጎረቤቶቻችሁ ምን ምን ታደርጉላቸዋላችሁ?
3. ጎረቤቶቻችሁ ለእናንተ ምን ምን ያደርጋሉ?
4. ካዳመጣችሁት ታሪክ ጋር የሚመሳሰል ሌላ ታሪክ ከቤተሰቦቻችሁ ጠይቃችሁ በመምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃላችሁ ተርኩ፡፡

**ተግባር ሁለት፡- ቃላት**

**ሀ. ከዚህ በታች ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሰረት ያደረጉ አረፍተ ነገሮች ቀርበዋል፤ በአረፍተ ነገሮቹ ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍች ስጡ፡፡**

1. ጉረብትና ለእርስ በእርስ ትስስር ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡
2. የሰርግ ስራውን በመረዳዳት እስከ ፍፃሜው አደመቁት፡፡
3. ማህበራዊ ህይወት የሚጎለብተው መልካም ጉርብትና ሲኖር ነው፡፡

4. አቶ አምሀ የተጣላን ጎረቤት <u>በማስታረቅ</u> ይታወቃል፡፡

5. ወይዘሮ ሀያት <u>አመት በዓል</u> ሲመጣ ለጎረቤቶቻቸው አስፈላጊውን እገዛ ሁሉ ያደርጋሉ፡፡

**ለ. ከዚህ በታች ከማዳመጥ ምንባብ ውስጥ ለወጡ ቃላት በምሳሌው መሰረት ተመሳሳይ ፍቾ ስጡ፡፡**

ምሳሌ፡- መልካም = ጥሩ፣ያማረ፣ሳቢ፣አስደሳች ወዘተ.

1. መቻቻል
2. መከባበር
3. መተማመን
4. ምስጉን
5. ማድመቅ

## ክፍል ሁለት፡- ንባብ

**‹‹ከሩቅ ዘመድ የቅርብ ጎረቤት››**



## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ከላይ ከቀረበው ምስል ምን ተረዳችሁ?
2. ‹‹ከሩቅ ዘመድ የቅርብ ጎረቤት›› የሚለውን አባበል ከዚህ በፊት ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?
3. ከርዕሱ ተነስታችሁ ምንባቡ ስለምን የሚያስረዳ ይመስላችኋል?

**‹‹ከሩቅ ዘመድ የቅርብ ጎረቤት››**

ጎረቤታሞች በበዓል ወቅት ቁርስ፣ምሳ፣እራት በየተራ እየተጠራሩ በመገባበዝ በደስታ አብረው ያሳልፋሉ፡፡ ተነፋፍቀው የተገናኙ ዘመዳሞች በተለያየ መንገድ ዝምድናና ወዳጅነት የፈጠሩ ሁሉ በዚህ መልኩ ተሰባስበው በሳቅ በጫወታ ያሳልፋሉ፡፡ የአብሮነት የአንድነትና ማህበራዊ ግንኙነቱ ማሳያ በሆነው በዓል ወቅት ብዙዎች ደስታቸውን ያጣጥማሉ፡፡ ሁሉም እንደየእምነቱ በዓሉን ቢያከብርም ክርስትያኑ ሙስሊም ጎረቤቱን፣ ሙስሊሙም እንዲሁ ክርስትያን ጎረቤቱን ጠርቶ ያለውን በወንድማማችነት መንፈስ የተገኘውን ሁሉ ተከፋፍለው በደስታ በዓሉን ያከብራሉ፡፡ ሰርግም ሲደግሱ እንዲሁ አይለያዩም፡፡ ስጦታቸውን በመያዝ ሄደው ይታደማሉ፡፡

**ጎረቤታሞች ዓመት በዓልን በጋራ ከማሳለፍ በተጨማሪ በምን በምን ሊረዳዱ ይችላሉ?**

እንዲህ በበዓል ወቅት ትስስሩ ይጠነክራል ለማለት እንጂ ሰዎች በጉርብትና አብረው ሲኖሩ አንዳቸው ለሌኛው የሚያሳዩት ፍቅርና መተሳሰብ ጠንካራ ነው፡፡ ጬኸት እንኳን ሲሰማ ጎረቤት ቀድሞ ይወጣል፡፡ ፀብም ከሆነ መሀል ገብቶ ይገላግላል፡፡ ድረሱልኝ ብሎም ከተጣራ ሰምቶ የሚተኛ ጎረቤት የለም፡፡ ከነአባባሉም ‹‹ከሩቅ ዘመድ የቅርብ ጎረቤት ይሻላል›› የሚል ነው፡፡ መተሳሰቡ ከዚህም አልፎ ልጅን በጉዲፈቻ ወስዶ እንደ ራስ ልጅ አድርጎ ወደማሳደግ

ይደርሳል፤ እዚህ ላይ መዘንጋት የሌለብን አንድ ሰው ልጅ በጉዲፈቻ ለማሳደግ ሲወስድ ዘር ጠይቆ ወይም ቆጥሮ አይደለም። በደም ከማይተሳሰረው ሰው ጋር በልጁ አማካኝነት ዝምድናውን ለማጠናከር ሲል የሚያደርገው ተግባር ነው።

**ለምለም መንግስቱ**

(አዲስ ዘመን ግንቦት 1 ቀን 2013 ዓ.ም የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዌብ ሳይት ላይ ለማስተማሪያነት እንዲመች ተደርጎ የተወሰደ)

## ተግባር አንድ፡- አንብቦ መረዳት

**ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ በቃላችሁ መልስ ስጡ፡**

1. ጎረቤታሞች እየተጠራሩ የሚገባበዙበት በምን ወቅት ነው?
2. በምንባቡ መሰረት የአብሮነትና የማህበራዊ ግንኙነት ማሳያ የሆነው ምንድን ነው?
3. በበዓላት ወቅት በወንድማማችነት መንፈስ የተገኘውን ሁሉ ተከፋፍለው ያከብራሉ የተባሉት እነማን ናቸው?
4. ጩኸት እንኳ ሲሰማ ቀድሞ ይደርሳል የተባለው ማን ነው?
5. ‹‹ከሩቅ ዘመድ የቅርብ ጎረቤት›› ከሚለው ምንባብ ምን ተረዳችሁ? ተራ በተራ ለክፍል ጓደኞቻችህ አስረዱ።

**ለ. ከዚህ ቀጥሎ ምንባቡን መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ለእያንዳንዳቸው ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል/ሆሄ ምረጡ።**

1. ጎረቤታሞች በበዓል ወቅት በምን በምን ጊዜ ሊጠራሩ ይችላሉ?

   ሀ. በቁርስ  ለ. በምሳ  ሐ. በእራት  መ. በሁሉም

2. ልጅን እንደ ራስ ልጅ ወስዶ ማሳደግ ምን ይባላል?
   ሀ. ጉዲፈቻ ለ. አምቻ ሐ. ጋብቻ መ. ጉልቻ

3. ‹‹በደም ከማይተሳሰሩት ጋር›› ሲባል ምን ለማለት ተፈልጎ ነው?
   ሀ. ዘመዳሞች ለ. ዝምድና የሌላቸው
   ሐ ወንድማማቾች መ. እህትማማቾች

4. ከሚከተሉት ውስጥ ጠንካራ ማህበራዊነት እንዲኖር የሚያስችለው የቱ ነው?
   ሀ. ፍቅር ለ. መከባበር ሐ. መተሳሰብ መ. ሁሉም

**ሐ. ከዚህ በታች በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ወይም ሀረጋት አውዳዊ ፍች ስጡ።**

1. ተነፋፍቀው የተገናኙ ቤተ ዘመድ ሁሉ ተሰባስበው <u>በሳቅ በጫወታ</u> በዓልን ያሳልፋሉ።
2. የአንድነትና ማህበራዊ ግንኙነት <u>ማሳያ</u> በሆነው በዓል ወቅት ብዙዎች ደስታቸውን ያጣጥማሉ።
3. በሠርግ ድግስ ወቅት <u>ታዳሚዎች</u> ስጦታ ይዘው ይሄዳሉ።
4. እዚህ ላይ <u>መዘንጋት</u> የሌለብን አንድ ሰው በጉዲፈቻ ልጅ ሲወሰድ ዘር ጠይቆ አይደለም።

## ተግባር ሁለት፡- አቀላጥፎ ማንበብ

ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ ድምጻችሁን ከፍ አድርጋችሁ መምህራችሁ በሚሰጣችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

## ፌኔትና ያዕቆብ

ፌኔትና ያዕቆብ የአካባቢያችን ልጆች ናቸው፡፡ ፌኔት በትምህርቷ በጣም ጎበዝ በመሆኗ የቤት ስራዋን በአግባቡ ሰርታ ትመጣለች፡፡ በዚህም የተነሳ መምህሮቿ በጣም ይወዷታል፡፡ ያዕቆብ ደግሞ ስለማያጠና የቤት ስራውንም በአግባቡ ስለማይሰራ መምህራኑ ሁልጊዜ ይቆጡታል፡፡ ፌኔት ይህንን ተመልክታ ያዕቆብን ‹‹አንተ ለምን አታጠናም? የቤት ስራህን ለምን ሰርተህ አትመጣም?›› ስትል ጠየቀችው፡፡ ያዕቆብም ‹‹ከእንግዲህ ወዲህ ጊዜዬን በአግባቡ በመጠቀም የቤት ስራዬንም ሰርቼ እመጣለሁ›› በማለት የፌኔትን ምክር ተቀብሎ በጋራ ማጥናት ጀመሩ፤ የቤት ስራቸውን አብረው መስራት ቀጠሉ፡፡ በዚህም የተነሳ ያዕቆብ በትምህርቱ ከቀን ወደ ቀን በከፍተኛ ሁኔታ እየተሻሻለ መጣ፡፡ በዚህም ምክንያት ሁለቱም ጓደኛሞች በሰፈሩም ሆነ በትምህርት ቤቱ የታወቁ አርዓያ ተማሪዎች መሆን ቻሉ፡፡

## ክፍል ሶስት፡-ቃላት

### ተግባር አንድ ፡- የቃላት ፍቺ

**ሀ. ለሚከተሉት በ "ሀ" ረድፍ ላሉት ቃላት ከ "ለ" ረድፍ ተመሳሳይ ፍች በመምረጥ አዛምዱ፡፡**

| <u>ሀ</u> | <u>ለ</u> |
|---|---|
| 1. መስተጋብር | ሀ. ደግ/መልካም |
| 2. ቅን | ለ. አታላይ/አጭበርባሪ |
| 3. ሸንጋይ | ሐ. ግንኙነት/ትስስር |
| 4. ተወዳጀ | መ. ተዛመደ/ ተፋቀረ |
| 5. አሰናዳ | ሠ. ሀሴት/ፈንጠዚያ |
| 6. ደስታ | ረ. አዘጋጀ/ ሰራ |

ለ. ቀጥሎ በ "ሀ" ረድፍ ላሉት ከ "ለ" ረድፍ ተቃራኒ ፍች በመምረጥ አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ሰጠ | ሀ. ራስጌ |
| 2. ባህላዊ | ለ. ቀማ |
| 3. ግርጌ | ሐ. ሰበሰበ |
| 4. ፍቅር | መ. ዘመናዊ |
| 5. በተነ | ሠ. መራራ |
| 6. ጣፋጭ | ረ. ጥላቻ |

ሐ. ምሳሌውን መሰረት በማድረግ በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያሉትን ውስብስብ ሆሄያት ለይታችሁ አውጡ፡፡

| ምሳሌ፡- ተጓዘ | ጓ |
|---|---|
| ተንኳኳ | ኳ |
| ላሟ | ሟ |

| ተ.ቁ | ቃላት | ውስብስብ ፊደላት |
|---|---|---|
| 1 | ሯጭ | |
| 2 | ፏፏቴ | |
| 3 | በኋላ | |
| 4 | ታንኳ | |

| | | |
|---|---|---|
| 5 | ቧንቧ | |

**መ. የሚከተሉትን ውስብስብ ሆሄያት በመጠቀም ቃላትን መስርቱ፡፡**

ምሳሌ፡- ሷ = ልብሷ

1. ጧ 2. ቋ 3. ሿ

4. ቷ 5. ኋ

## ክፍል አራት፡- ጽህፈት

ማስታወሻ

ስርዓተ ነጥቦች

በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ የተለያዩ ስርዓተ ነጥቦች አሉ፡፡ እነዚህን ስርዓተ ነጥቦች ጥቅም ላይ የምናውላቸው በፅሁፍ ወቅት ሲሆን በፅሁፉ ለአንባቢ ግልፅ የሆነ መልዕክትን ለማስተላለፍ ያግዛሉ፡፡ በፅሁፍ ውስጥ ተዘውትረው ጥቅም ላይ የሚውሉት ስርዓተ ነጥቦች የሚከተሉትን ይመስላሉ፡፡

1.ጥያቄ ምልክት (?) ይህ ስርዓተ ነጥብ ጥያቄያዊ አረፍተ ነገሮችን በማቅረብ ያገለግላል፡፡ **ምሳሌ**፡- መቼ መጣህ?

2. ነጠላ ሰረዝ (፣)

ይህ የስርዓተ ነጥብ ምልክት የሚያገለግለው ተመሳሳይነት ያላቸውን ተከታታይ ነገሮች በምንዘረዝርበት ጊዜ በመካከላቸው ለመለያነት በመግባት ያገለግላል፡፡

**ምሳሌ**፡- ብርቱካን፣ሙዝ፣ ፓፓዬ እና አናናስ ጠቃሚ ፍራፍሬዎች ናቸው፡፡

3.ቃለ አጋኖ (!) ይህ የስርዓተ ነጥብ ምልክት ለሰዎች ማስጠንቀቂያበምንናገርበትጊዜ ወይም አድናቆታችንን በምንገልፅበት

ጊዜ በፅሁፍ ውስጥ የምንጠቀምበት ነው፡፡

**ምሳሌ**፡- ተጠንቀቁ!

ድንቅ ! እንዴት ያለ ጎበዝ ልጅ ነው፡፡

4.ትዕምርተ ጥቅስ (‹‹ ››) ይህ የስርዓተ ነጥብ ምልክት የሚያገለግሉ ሰዎች የፃፉትን ወይም የተናገሩትን በፅሁፍ ውስጥ ራሳችን ከጻፍነው ሀሳብ ለይተን የምናመለክትበት ነው፡፡

**ምሳሌ**፡- መምህሩ ‹‹በርትታችሁ አጥኑ›› ሲሉ መከሩን፡፡

**ሀ. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የገቡትን ስርዓተ ነጥቦች ለይታችሁ ፃፉ፡፡**

1.መቼ ትመጫለሽ?

2. እሱ ጎበዝ ተማሪ ነው፡፡

3. ድንቅ ! እንዴት ታምራለች፡፡

4.ታምራት የስምንተኛ ክፍል ተማሪ ነው፡፡

5.እሰይ! በጉጉት የሚጠብቀው የህዳሴው ግድባችን ሊጠናቀቅ ነው፡፡

**ለ. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች በተገቢው ስርዓተ ነጥብ አሟልታችሁ ፃፉ፡፡**

1.ይገርማል በጣም ግዙፍ ነው

2.ስርተን መለወጥ የምንችልባት ውብ ሀገር አለችን

3.ባቄላ አተር አኩሪ አተርና ሽምብራ የጥራጥሬ እህሎች ናቸው፡፡

4.የአማርኛ መምህራችን በርትቶ ያጠና ተማሪ ጥሩ ውጤት ያመጣል እያለ በተደጋጋሚ ይመክሩናል፡፡

5.እጅን በተደጋጋሚ በሳሙና መታጠብ ኮሮና ቫይረስን ለመከላከል ከሚያስችሉ መንገዶች አንድ ነው፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትዕዛዙን መሰረት በማድረግ መልሳችሁን ስጡ፡፡**

1.ማህበራዊ ግንኙነትን ሊያጎለብቱ የሚችሉ ጉዳዮችን ከተለያዩ መገናኛ ብዙሃን አዳምጣችሁ በመፃፍ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

1. ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቺ ስጡ፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ. መወዳጀት | ሐ. አብሮነት |
| ለ. መለገስ | መ. ታጋሽነት |

2. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የተጓደሉትን የስርዓተ ነጥብ ምልክቶች አሟልታችሁ ፃፉ፡፡

ሀ. የሒሳብ መምህራችን የቤት ስራችሁን በአግባቡ ስሩ አሉ፡፡

ለ.ደብተር እርሳስ እስክሪብቶ መፅሐፍ የትምህርት መሳሪያዎች ናቸው፡፡

ሐ.የአንድነት ፓርክ ሊጎበኝ የሚገባው የመዝናኛ ስፍራ ነው፡፡

መ.ድንቅ የአካል ጉዳተኝነቱ ሳያግደው ምርጥ የፈጠራ ውጤት ሰርቶ አቀረበ

# ምዕራፍ ሶስት


## ተረት

የምራፉ አላማዎች፣ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ያዳመጣችሁትን ተረት ትተርካላችሁ።
- በተረት ውስጥ ያሉትን ዋና ገጸ ባህሪያት ትናገራላችሁ።
- ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ ጠብቃችሁ ድምጻችሁን ከፍ አድርጋችሁ አጭር ተረት ታነባላችሁ።
- የታሪኩን ዋና ሀሳብ ትፅፋላችሁ።
- በምንባቡ ውስጥ ያሉትን አዳዲስ ቃላት ፍች ትገምታላችሁ።
- በተለያዩ ፅሁፎች ውስጥ ያሉ ስሞችን ትለያላችሁ።

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

### ሰማዕቷ እናት



## ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ስዕሉን ስትመለከቱ ምን የሚል ተረት አስታወሳችሁ?

2. ‹‹ሰማዕቷ እናት›› የሚለው ተረት ስለምን የሚነግረን ይመስላችኋል?

## ተግባር አንድ፡- አዳምጦ መረዳት

**ሀ. ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

1. ልጁ በድርጊቱ የተፀፀተው በምን ምክንያት ነው?
2. እናት የገዛ ልጇ ‹‹ሰራተኛዬ ናት›› እያለ ሲያስተዋውቃት ቅር ያልተሰኘችው ለምንድን ነው?
3. በተረቱ ውስጥ የተጠቀሱት ዋና ዋና ባለታሪኮች (ገፀ ባህሪያት) እነ ማን ናቸው?
4. በተረቱ ውስጥ ‹‹እናት ጥራ ግራ ልጇን ትመግበው ነበር›› ይላል፡፡ ልጅን ተንከባክቦ ማሳደግና መመገብ የእናት ሀላፊነት ብቻ ይመስላችኋል? ለምን? ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ ተነጋገሩበትና ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
5. ልጁ ስለእናቱ እውነተኛ ታሪክ ቢያውቅ ይህን የሚያደርግ ይመስላችኋል?

**ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መምህራችሁ በሚያደራጇችሁ ቡድን ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሀሳብ በፅሁፍ አስፍሩ።**

1. በተረቱ ውስጥ ‹‹የእሷ ውበት ከእኔ ላይ ነው፤ የእኔ ጠባሳ ደግሞ እሷ ላይ ነው›› የሚለው ሀሳብ የሚያስተላልፈውን መልዕክት በፅሁፍ መልሱ።
2. ‹‹ሰማዕቷ እናት›› የሚለው ተረት የሚያስተላልፈውን ፍሬ ሀሳብ በአራት አረፍተ ነገር በፅሁፍ ግለፁ።
3. ከዚህ ተረት ጋር የሚዛመድ እውነተኛ ታሪክ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? የምታውቁትን በፅሁፍ አስፍሩ።

**ተግባር ሁለት፡- ቃላት**

**ሀ. ከላይ ካዳመጣችሁት ተረት ውስጥ ለወጡት አዳዲስ ቃላትና ሀረጋት ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ቀጥተኛ ፍቺ ስጡ።**

**ምሳሌ፡-** ተመለከተ = አየ

ባልንጀራ = ጓደኛ

1. አወጋችው
2. ሰማዕቷ
3. ጠቅልዬ
4. ጥራ ግራ
5. ደፋ ቀና
6. መተኪያ የሌለው

**ለ. ለሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት ተቃራኒ ፍቻቸውን ስጡ።**

1. መስራት
2. መልከኛ
3. ክፉኛ ተጎዳሁ
4. ይገኼ ቀረሁ
5. ቅር መሰኘት

**ሐ. ለሚከተለት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ከሰጣችሁ በኋላ በፍቺው አረፍተ ነገር መስርቱ፡፡**

**ምሳሌ፡-** መከወን = መፈፀም

- ስራችንን በጊዜ መፈፀም ተገቢ ነው፡፡

1.ተቃጠለ 2.ተበላሸ 3.ሳተርፍህ

4 የተከበረ 5.መፀፀት

## ክፍል ሁለት፡- ንግግር

### ተግባር አንድ፡- እንቆቅልሽ

**ሀ.ከዚህ በታች በቡድን በመሆን የምትጠያየቁት እንቆቅልሽ ቀርቦላችኋል፡፡ መምህራችሁ በሚያደራጇችሁ ቡድን መሰረት እንቆቅልሹን ተጠያየቁ፡፡ እንቆቅልሹን ስትጠያየቁ አንዱ ጠያቂ ሌሎቻችሁ መላሽ ሁኑ፡፡ መላሽ የነበረው ደግሞ በተራው ጠያቂ ይሁን፡፡ የእንቆቅልሽ ሂደቱን ጠብቃችሁ ተጠያየቁ፡፡**

**ምሳሌ፡-**

**ጠያቂ** = እንቆቅልሽ/ህ

**መላሽ** = ምን አውቅልሽ/ህ

**ጠያቂ** = በአረንጓዴ አውቶቢስ ውስጥ ነጫጭ ተሳፋሪዎች

**መላሽ** = ቃሪያ

1. በልቶ የማይጠግብ ያገኘውን የሚውጥ

2. ትንሽ ምላጭ ሀገር ትላጭ

3. እሷጥቁር ልጆቿ ነጫጭ

4. አፍ የላት ትናገራለች እግር የላት ትሮጣለች

5. ሲሄድ ሺህ ገዳይ ሲመለስ ሺህ ገዳይ

## ክፍል ሶስት፡- ንባብ

ዛፎች



## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ስዕሉን ተመልከቱና የተረዳችሁትን ሃሳብ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

2. ‹‹ዛፎች›› የሚለውን ርዕስ ስታነቡ ምን አስታወሳችሁ?

## ዛፎች

ከዕለታት አንድ ቀን በዓለም ዙሪያ ያሉ ዛፎች ተሰባስበው ስለችግሮቻቸው ይወያዩ ነበር፡፡ ከመሃከላቸውም አንዱ ዛፍ እንዲህ አለ ‹‹የእኛ ትልቁ ችግር የደን መመንጠር ነው፡፡ ይህም ድርጊት የሚፈፅምብን መጥረቢያ በተባለ መሳሪያ ነው፡፡ ስለዚህ ጠላታችን የሆነውን መጥረቢያን ማጥፋት አለብን›› አለ፡፡ ብዙዎቹም በዚህ ሃሳብ ዙሪያ አሰተያየት በመስጠት ‹‹መጥረቢያ ነው የሁልጊዜ የስቃያችን ምንጭ ይቆርጠንና ቢያሻው ለማገዶ አሊያም ለቤት እቃ መስሪያ፤ አረ ምኑ ቅጡ! ስለዚህ አንድ መላ ፈልገን ይህንን ጠላታችንን ማጥፊት አለብን›› ብለው መከሩ፡፡

### ቀጥሎ ዛፎቹ ምን የሚሉ ይመስላችኋል?

አንድ ባህር ዛፍም እጁን አውጥቶ ‹‹ጠላታችን ግን መጥረቢያ አይመስለኝም›› አለ፡፡ በዚህን ጊዜ ሁሉም ዛፎች ወደርሱ ዞረው ‹‹እንዴ! ምን ማለትህ ነው? እሱ ካልሆነ ታዲያ ማን ሊሆን ይችላል?›› ብለው ጮሁበት፡፡ ባህር ዛፍም ንግግሩን እንዲህ ሲል ቀጠለ ‹‹አያችሁ እኔ ከልቤ ነው የምላችሁ ጠላታችን መጥረቢያ አይደለም እኛው ራሳችን ነን፡፡ ሁላችንም መጣመም ትተን ቀጥ ብለን ብናድግ ኖሮ መጥረቢያ እጀታ አይኖረውም፤ እኛም ከመቆረጥ እንድን ነበር፡፡ ስለዚህ ከዚህ በኋላ ሁላችንም ሳንጣመም ቀጥ ብለን በማደግ መጥረቢያውን እጀታ ማሳጣት አለብን፡፡››

በዚህ ጊዜ ሁሉም ዛፎች አጨበጨቡለት፡፡

አብርሃም እንደ ሻው፣ ኢትዮጲስ ቁጥር ሁለት፣ (ዓመተ ምህረቱ ያልታወቀ) ለማስተማሪያነት ተሻሽሎ የቀረበ

## ተግባር አንድ፡- አንብቦ መረዳት

**ሀ. ለሚከተለት ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ በቃላችሁ መልስ ስጡ፡፡**

1. የምንባቡን ዋና ሀሳብ በቃል ተናገሩ፡፡
2. ደኖች የሚመነጠሩት በምንድን ነው?
3. በአለም ዙሪያ ያሉት ዛፎች ተሰብስበው የተወያዩት ምን ችግር ገጥሟቸው ነው?
4. የዛፎች መቆረጥ ችግሩ የዛፎች ነው ወይስ የሰው ልጅ ይመስላችኋል? ተወያዩበት፡፡
5. ሁላችንም መጣመም ትተን ቀጥ ብለን ብናድግ ኖሮ መጥረቢያ እጀታ አይኖረውም ሲል ምን ማለት ፈልጎ ይመስላችኋል?

**ለ. በምንባቡ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በፅሁፍ መልሱ፡፡**

1. በምንባቡ ውስጥ ዛፎቹ ምንን ወክለው የቀረቡ ገፀባህሪያት ናቸው?
2. ባህር ዛፍ “ጠላታችን መጥረቢያ አይደለም እኛው እራሳችን ነን” ያለው ለምንድን ነው? አንድ ነገር እንዴት ለራሱ ጠላት ይሆናል? በቡድን ተወያዩበትና የደረሳችሁበትን ፅፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡
3. ምንባቡን እንደገና አንድ ጊዜ በፅሞና ደግማችሁ በማንበብ የተረዳችሁትን የምንባቡን ፍሬ ሃሳብ በሶስት አረፍተ ነገሮች ፃፉ፡፡

## ተግባር ሁለት፡- ቃላት

ቀጥሎ በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡

1. ተክል ማደግ እንዲችል ውሃና አየር ያስፈልገዋል፡፡
2. የደኖች መመንጠር ለአንድ ሀገር እድገት ፀር ነው፡፡
3. ገንዘብን ያለ አግባብ ማጥፋት ለድህነት ያጋልጣል፡፡
4. የሰው ልጅ ህይወት በትራፊክ አደጋ እንዳይቀጠፍ መላ ሊያበጁለት ይገባል፡፡
5. ተማሪዎቹ በትምህርት ቤታቸው ንፅህና አጠባበቅ ላይ ተገናኝተው መከሩ፡፡
6. መጣመም ትተን ቀጥ ብለን ብናድግ መጥረቢያ እጄታ አይኖረውም

## ተግባር ሶስት፡- አቀላጥፎ ማንበብ

ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ ትዕዛዝ መሰረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ፡፡

| ጭልፊቷ |
|---|
| ጭልፊቷ ጫጩት ፈለፈለችና መግባ ታቅፋ አሳደገች፡፡ ጫጩቷ አድጋ ክንፍ ከበቀለላት በኋላ ለመብረር ብቃት ያላት መሆኗን አረጋገጠች፡፡ ከዚያም እናቷን ‹‹እማዬ እንግዲህ ለመብረር እየተዘጋጀሁ ነው፤ ከመብረሬ በፊት ግን የምትመክሪኝ ነገር ካለ |

ካሁኑ ንገሪኝ›› አለቻት። እናትም ‹‹ሰዎች አንችን አይተው ጎንበስ ያሉ እንደሆነ ሰላምታ ነው ብለሽ ቀረብ ቀረብ እንዳትያቸው ። ምክንያቱም ከአንገታቸው ጎንበስ የሚሉት ድንጋይ አንስተው ክንፍሽን ሊያደቁልሽ ነው ››በማለት መከረቻት ።

## ክፍል አራት፡— ጽህፈት

### ተግባር አንድ፡- መፃፍ

**ሀ. ከዚህ በታች በቀረቡት ቃላት ምሳሌውን መሰረት በማድረግ አረፍተ ነገር በፅሁፍ መስርቱ።**

**ምሳሌ፡-** ተረት = የሶስተኛ ክፍል ተማሪዎች ተረት ይወዳሉ።

1. ክንፍ　　2. ጭልፊት　　3. ምክር

4 በረረ　　5.ብቃት

**ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በትዕዛዙ መሰረት በፅሁፍ መልሱ።**

1. የተለያዩ የተረት መፅሐፎችን ፈልጋችሁ አንብቡና ተረቱን በመፃፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።
2. ጥንድ ጥንድ በመሆን አንድ የምታውቁትን ተረት መርጣችሁ ተረቱን በራሳችሁ አገላለጽ መልሳችሁ ጻፉ።

## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

### ተግባር አንድ፡- ስሞችን መለየት

**ማስታወሻ**

ስም የተለያዩ ነገሮች መጠሪያ ነው፡፡ የሰዎች፣ የቁሳቁሶች፣ የሀገሮች፣ የነገሮች፣ የቦታዎች ወዘተ. መጠሪያ ወይም ስያሜ ስም ይባላል፡፡

**ለምሳሌ፡-**

- ✓ የቁሳቁሶች፡- ቤት፣ መኪና፣ አልጋ፣ በርሳ፣ ጫማ፣ …
- ✓ የሰዎች ፡- ኑሪያት፣አክመል፣ ሄርሜላ፣አስራት…
- ✓ የከተሞች፡- ዲላ፣አርባ ምንጭ፣ሶዶ፣ሆሳእና…
- ✓ የቦታዎች፡- ገበያ፣ ስታድዬም፣ ቤተክርስቲያን፣ መስጊድ

**ሀ. ከዚህ በታች በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ የተጠቀሱትን ስሞች ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ለይታችሁ አውጡ፡፡**

**ምሳሌ፡-**

1. አስቴር ነገ ኳስ ሜዳ ትሄዳለች፡፡ (አስቴር ፣ ኳስ ሜዳ) እነዚህ በቅንፍ ውስጥ የቀረቡት ቃላት ስሞች ናቸው፡፡
2. ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙት ትላልቅ ወንዞች መካከል አባይ፣ ባሮ፣አዋሽ ይጠቀሳሉ፡፡ (ኢትዮጵያ፣ወንዞች፣አባይ፣ባሮ፣አዋሽ) እነዚህ በቅንፍ ውስጥ ተለይተው የቀረቡት ቃላት ስሞች ናቸው፡፡

1. የሶስተኛ ክፍል ተማሪዎች ጎበዞች ናቸው፡፡
2. ያሬድ፣ ቤት፣መኪናና ሳይክል ገዛ፡፡
3. ጥጥ የባህል ልብስ ይሰራበታል፡፡

4.ተማሪ፣መምህርና ርዕሰ መምህር ትምህርት ቤት ውስጥ ይገኛሉ፡፡

5. በግ፣ፍየል፣ዶሮ፣ድመትና ውሻ የቤት እንስሳት ናቸው፡፡

**ለ. ከዚህ በታች በቀረበው ሰንጠረዥ ውስጥ የቀረቡትን ስሞች የሰው፣ የቁሳቁስና የቦታ እያላችሁ በራይት ምልክት አሳዩ፡፡**

| ተ.ቁ | ስሞች | የሰው | የቁሳቁስ ስሞች | የቦታ ስሞች |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ጂንካ | | | ✓ |
| 2 | ቴሌቭዥን | | ✓ | |
| 3 | ፌቨን | ✓ | | |
| 4 | ወልቂጤ | | | |
| 5 | ወንበር | | | |
| 6 | ሀናን | | | |
| 7 | ኮንሶ | | | |
| 8 | ይስሀቅ | | | |
| 9 | ጠረጴዛ | | | |
| 10 | መፅሀፍ | | | |
| 11 | ልብስ | | | |

## የክለሳ ጥያቄዎች

**ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጡ፡፡**

1. አንድ የልጆች ተረት አዳምጣችሁ በመምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል ተርኩላቸው፡፡
2. የተረት መፅሐፍ ፈልጋችሁ በማንበብ ባለታሪኮቹን ፅፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡
3. ለሚከተሉት ቃላት ቀጥተኛ ፍቺ ስጡ፡፡

   ሀ. መተረክ ለ. መሰባሰብ ሐ. መመካከር
4. አምስቱን የሰው ልጅ የስሜት ህዋሳት ስም ፃፉ፡፡

**ለ. ከዚህ በታች የሰፈሩትን ግሶች በመጠቀም ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡**

1. በላ 2. ወረደ 3.ጠለፈ

4 አወዛወዘ 5. ሄደ 6. ገባ

# ምዕራፍ አራት

## የጊዜ አጠቃቀም

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**


- ስለሰዓት አጠቃቀም አዳምጣችሁ ትናገራላችሁ፡፡
- ፅሑፉን አንብባችሁ መልዕክቱን ትናገራላችሁ፡፡
- በቃል እየተነገራችሁ አረፍተ ነገሮችን ትፅፋላችሁ፡፡
- የተውሶ ቃላትን ትለያላችሁ፡፡
- ግሶችን ትለያላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

‹‹የዛሬ አበባዎች የነገ ፍሬዎች››



የግድግዳ ሰዓት፣



| ቀን | ስኞ | ማክ | ረቡዕ | ሐሙስ | አርብ | ቅዳሜ | ዕሁድ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| እንግ | 10፡00-10፡50 | | 10፡00-10፡50 | | 10፡00-10፡50 | | 10፡00-10፡50 |
| አማርኛ | | 10፡00-10፡50 | | 10፡00-10፡50 | | 10፡00-10፡50 | |
| ሒሳብ | 11፡00-10፡50 | | 11፡00-10፡50 | | 11፡00-10፡50 | | 11፡00-10፡50 |
| ሳይንስ | | 11፡00-10፡50 | | 11፡00-10፡50 | | 11፡00-10፡50 | |
| ዕ.ትወና | 1፡00-1፡50 | | 1፡00-1፡50 | | 1፡00-1፡50 | | 1፡00-1፡50 |

የጥናት ፕሮግራምን የሚጠቁም ሰንጠረዥ

### የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ስዕሉን በመመልከት የተረዳችሁትን ሃሳብ ለመምህራችሁ

ተናገሩ።

2. ‹‹የዛሬ አበባዎች የነገ ፍሬዎች›› በሚል ርዕስ የቀረበው ምንባብ ምን መልዕክት የሚያስተላልፍ ይመስላችኋል?

**ተግባር አንድ፡- አዳምጦ መረዳት**

***ሀ. ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።***

1. በአንድ ቀን ውስጥ ስንት ሰዓታት አለ?

2. የነገ ሀገር ተረካቢዎች የተባሉት እነማን ናቸው?

3. ካዳመጣችሁት ምንባብ የተረዳችሁትን ሃሳብ ለመምህራችሁ ተናገሩ።

4. ሀገራችን የምን የምን ሙያ ባለቤት የሆነ ትውልድ ያስፈልጋታል?

5. አንድ ተማሪ ጊዜውን በአግባቡ ከፋፍሎ ባይጠቀም ምን የሚሆን ይመስላችኋል?

**ተግባር ሁለት፡- ቃላት**

**ከዚህ በታች በ "ሀ" ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ከ "ለ" ረድፍ ተመሳሳይ ፍቺቸውን በመምረጥ አዛምዱ።**

| ***<u>ሀ.</u>*** | ***<u>ለ.</u>*** |
|---|---|
| 1. በአግባቡ | ሀ. ማነፅ |
| 2. መበርታት | ለ. በተገቢው |
| 3. መገንባት | ሐ. መጠንከር |
| 4. መሰረት | መ. መስክ |
| 5. ከፋፍሎ | ሠ. መገንዘብ |
| 6. መረዳት | ረ. መነሻ |
| 7. ዘርፍ | ሰ. መድቦ |

**ተግባር ሶስት፡- መፃፍ**

***ሀ. ከዚህ በታች በቀረቡት ቃላት ዓረፍተ ነገር በፅሁፍ መስርቱ።***

1. ሰሌዳ 2. ትውልድ 3. ህይወት

4 ልምድ 5.ብቃት

**ለ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትዕዛዙን መሰረት በማድረግ መልሳችሁን በፅሑፍ አስፍሩ።**

1. ጊዜን በአግባቡ መጠቀም እንዴት ውጤታማ ሊያደርግ እንደሚችል በሶስት አረፍተ ነገሮች ፃፉ።
2. አንድ ተማሪ ለትምህርቱ ጠንካራ ፍላጎት ባይኖረው ምን ሊሆን ይችላል? ሀሳባችሁን በሁለት አረፍተ ነገር በፅሁፍ አስፍሩ።

## ክፍል ሁለት፡ ንግግር

### ተግባር አንድ፡- ምልልስ

**ሀ. ተማሪዎች ከዚህ በታች የቀረበውን ምሳሌ መሰረት በማድረግ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ ትዕዛዝ መሰረት ጥንድ ጥንድ በመሆን ንግግር አድርጉ።**

**ምሳሌ፡-**

አቤኔዘር፡- ጠዋት ስንት ስዓት ትነሻለሽ?

ቨሮኒካ፡- አስራ ሁለት ሰዓት ተኩል። አንተስ?

አቤኔዘር፡- ለአንድ ሩብ ጉዳይ። ትምህርት ቤት ስንት ሰዓት ትደርሻለሽ?

ቬሮኒካ፡- አንድ ሰዓት ተኩል። አንተ ትቀድመኛለህ?

አቤኔዘር፡- አዎ እኔ እቀድምሻለሁ። አንድ ሰዓት ከሩብ እደርሳለሁ። ቤታችን ቅርብ አይደል።

## ክፍል ሶስት፡- ንባብ

‹‹ናርዶስና ልዑል››



## ናርዶስና ልዑል

ናርዶስና ልዑል ወንድምና እህት ናቸው፡፡ ሁለቱም የሶስተኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆኑ ጊዜያቸውን ለትምህርት፣ ለጥናት፣ ለመዝናናትና ቤተሰብን ለማገዝ በማለት ከፋፍለው መድበዋል፡፡ ለትምህርት በመደቡት ጊዜያቸው ሰዓታቸውን አክብረው ወደትምህርት ቤት በመሄድ በትምህርት ገበታቸው ላይ ይገኛሉ፡፡ በክፍል ውስጥም እያንዳንዱን የትምህርት አይነት በንቃት ይከታተላሉ፡፡ መምህሮቻቸው የሚሰጧቸውን የቤት ስራ በአግባቡ ሰርተው ስለሚመጡ ሁል ጊዜም በትምህርታቸው ቀዳሚ ናቸው፡፡ ከትምህርት ቤት ያለበቂ ምክንያት መቅረት አይወዱም፡፡ የትምህርት ጊዜን ማክበር ለህይወታቸው ትልቅ ትርጉም እንዳለው ያውቃሉ፡፡

**ከላይ ከቀረበው ከነናርዶስና ከልዑል ታሪክ ምን ተረዳችሁ? ቀጥሎስ ስለ ምን የሚቀርብ ይመስላችኋል?**

ናርድስና ልዑል ከትምህርት ቤት ሲመለሱ የደንብ ልብሳቸውን ቀይረው ትንሽ እረፍት ካደረጉ በኋላ ማጥናት ይጀምራሉ፡፡ የተሰጣቸውንም የቤት ስራ አብረው ይሰራሉ፡፡ ያልገባቸውንም

ነገር ይጠያየቃሉ፡፡ ወላጆቻቸው የገዙላቸውን አጋዥ መፅሐፎች ያነባሉ፡፡ በሚያጠኑበት ጊዜ ሁለቱም ያልገባቸው ነገር ካለ መዝግበው በመያዝ መምህሮቻቸውን ይጠይቃሉ፡፡
የጥናት ጊዜያቸውንና የቤት ስራቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ከጓደኞቻቸው ጋር ይጫወታሉ፡፡ በትርፍ ጊዜያቸው ወደመዝናኛ ስፍራ ይሄዳሉ፡፡ ባላቸው ትርፍ ጊዜ አቅማቸው የሚፈቅደውን ስራ በማገዝ ከቤተሰብ ጋር ያሳልፋሉ፡፡

## ተግባር አንድ፡- አንብቦ መረዳት

**ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ በቃል መልስ ስጡ፡፡**

1. በክፍል ውስጥ እያንዳንዱን ትምህርት በንቃት መከታተል ለምን ያስፈልጋል?
2. ከትምህርት ቤት ያለ በቂ ምክንያት መቅረት ሊያስከትለው የሚችለው ጉዳት ምንድን ነው?
3. ናርዶስና ልዑል ጊዜያቸውን በአግባቡ ይጠቀማሉ ብላችሁ ታስባላችሁ? ለምን?
4. እናንተ ብትሆኑ ስታጠኑ ያልገባችሁን ነገር ማንን ትጠይቃላችሁ?

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ በፅሑፍ መልስ ስጡ፡፡**

1.‹‹ናርዶስና ልዑል››ከሚለው ምንባብ የተረዳችሁትን ፍሬ ሃሳብ በአራት አረፍተነገሮች በመጻፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

2. እናንተ ጊዜያችሁን እንዴት እየተጠቀማችሁበት እንደሆነ በአምስት አረፍተ ነገሮች ፃፉ፡፡

**ተግባር ሁለት፡- ቃላት**

**ከዚህ በታች በሰንጠረዡ ውስጥ ከቀረቡት ቃላት በመምረጥ የተጓደሉትን አረፍተ ነገሮች አሟልታችሁ ፃፉ፡፡**

| | | |
|---|---|---|
| ጥቃቅን | ጢም ብሎ | ስራ |
| ትኩረት | መምህር | ጥቅም |

1. ውሃው_____________________ሞላ፡፡
2. ________________የእውቀት አባት ነው፡፡
3. _______________የሰው ልጆች ህልውና ነው፡፡
4. _______________ጉዳዮች ከአላማችን ሊያስቀሩን አይገባም፡፡
5. ጊዜን በአግባቡ__________________ላይ ማዋል ተገቢ ነው፡፡
6. በህይወታችን________________መስጠት ያለብን ለወሳኝ ጉዳዮች ነው፡፡

**ክፍል አራት፡- ቃላት**

**ተግባር አንድ፡ የተውሶ ቃላት**

| |
|---|
| ቴሌቭዥን፣ ጳጳስ፣ ሬዲዮ፣ ኢንተርኔት፣ አባወራ፣ ቀበቶ፣ ሞባይል ወዘተ. አማርኛ ቋንቋ ከሌሎች ቋንቋዎች የተዋሳቸው ቃላት ናቸው፡፡ |

**ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ከዚህ በታች የቀረቡትን የተውሶ ቃላት በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን መስርቱባቸው፡፡**

**ምሳሌ፡-**

ሀ. እኔ <u>ቴሌቭዥን</u> መመልከት እወዳለሁ፡፡

**ለ.** አባቴ <u>ሬዲዮ</u> እያዳመጠ ነው፡፡

ሐ. ታሪኩ የቤቱ <u>አባወራ</u> ነው፡፡

| | | |
|---|---|---|
| 1. ፖሊስ | 2. እንሰት | 3. ዩኒቨርሲቲ |
| 4 ፖስታ | 5. ሰንጋ | 6. ፓስታ |

## ክፍል አምስት፡- ፅህፈት

### ተግባር አንድ፡- መፃፍ

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ በፅሑፍ አስፍሩ፡፡**

1.እያንዳንዳችሁ ከጠዋት እስከ ማታ የምታከናውኗቸውን ተግባራት በቅደም ተከተል ፃፉ፡፡

2. ‹‹ጊዜ ወርቅ ነው›› የሚለው አባባል ምን መልዕክት እንደሚያስተላልፍ ሰዎችን ጠይቃችሁ ፅፋችሁ በመምጣት ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

**ለ. መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን አረፍተ ነገሮች አዳምጣችሁ በመፃፍ ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡**

## ክፍል ስድስት፡-ሰዋስው

### ተግባርአንድ፡- ግሶችን መለየት

ማስታወሻ

ግስ፡-በአረፍተነገር መጨረሻ በመግባት አረፍተ ነገርን የሚያስር ወይም የሚቋጭ የቃል አይነት ነው፡፡

**ምሳሌ፡-**

ሀ. ታማኝነት የመልካም ዜጋ መገለጫ <u>**ነው**</u>፡፡

ለ. ተማሪዎች ንፅህናቸውን <u>**ይጠብቃሉ**</u>፡፡

ሀ. ባለፈው ምዕራፍ ስለስሞች ተምራችኋል፡፡ የተማራችሁትን በማስታወስ ከዚህ በታች ከቀረቡት ስሞች እየመረጣችሁ በሰንጠረዡ ውስጥ በአይነት መድቧቸው፡፡

| |
|---|
| ፓፓዬ፣ ጫሞ፣ መንደሪን፣ ፍየል፣ ማንጎ፣ በግ፣ ዲላ፣ ሎሚ፣ ሃና፣አርባ ምንጭ፣ ነስረዲን |

| የፍራፍሬ ስሞች | የሃይቅ ስሞች | የእንስሳት ስሞች | የቦታ ስሞች | የሰው ስሞች |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |
| | | | | |

ለ. ከዚህ በታች በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ግሶች በማስመር ለዩ፡፡

1. አዳም ጎበዝ ሀኪም ነው፡፡
2. የአድዋ ድል ዘላለም ሲዘከር ይኖራል፡፡
3. ከተማችን የተለያዩ ብሄር ብሔረሰቦች መኖሪያ ናት፡፡
4. ኮምፒዩውተር የተለያዩ ስራዎችን ለመስራት ያስችላል፡፡
5. በውይይት ወቅት የሰዎችን ሀሳብ መረዳት ያስፈልጋል፡፡

ሐ. ከዚህ በታች በሰፈሩት የቃላት ዝርዝር ውስጥ ግስ የሆኑትን ለይታችሁ አስምሩባቸው፡፡

1. መኪና፣ ነበር፣ ይሆናል፣ ጂንካ፣ ክፉኛ
2. ፃፈ፣ መጓጓዣ፣ አቀረበ፣ ሞባይል፣ ደግ
3. ሶስተኛ፣ ገለጠ፣ ሶዶ፣ ጊዜ፣ ተጠቀመ
4. ስሩ፣ ሚዛን፣ አገዘ፣ አማርኛ፣ ጠረጴዛ
5. ሻይ፣ ናቸው፣ ሳይንስ፣ ጠጣ፣ ጎበዝ

## የክለሳ ጥያቄዎች

**ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጡ።**

1.ጊዜን በአግባቡ መጠቀም የሚሰጠውን ጠቀሜታ ወላጆቻችሁን ጠይቃችሁ በመምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃላችሁ አቅርቡ።

2. እያንዳንዳችሁ የጊዜ አጠቃቀማችሁን በተመለከተ ፅፋችሁ በመምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።

3. አማርኛ ቋንቋ ውስጥ በውሰት የገቡ አምስት ቃላት ፃፉ።

4. በሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ግሶች ለ ይታችሁ አስምሩባቸው።

ሀ. እህቴ ልብሷን አጠበች።

ለ. ልጁ በጠዋት ተነስቶ ቁርሱን በላ።

ሐ. ቅድስት ፀጉሯን አበጠረች።

መ. ጊቤ ትልቅ ወንዝ ነው።

ሠ.አለሙ በፍጥነት አነበበ።

**ለ. ከዚህ በታች የሰፈሩትን ግሶች በመጠቀም ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ።**

| | | |
|---|---|---|
| 1. በላ | 2. ወረደ | 3. ጠለፈ |
| 4. አወዛወዘ | 5. ሄደ | 6. ገባ |

# ምዕራፍ አምስት

## መጓጓዣ

### ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- የተሰጣችሁን ምንባብ መሰረት ያደረገ ዘገባ ታቀርባላችሁ፡፡
- የተሰጣችሁን ምንባብ በጥልቀት በማንበብ ከተጨባጭ ህይወታችሁ ጋር ታገናኙታላችሁ፡፡
- የተዘበራረቁ አረፍተ ነገሮችን አስተካክላችሁ ትፅፋላችሁ፡፡
- የስም ገላጮችን ትለያላችሁ፡፡
- ለቃላት ፍች ትሰጣላችሁ፡፡

### የመጓጓዣ አይነቶችና አገልግሎታቸው



### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ስዕሉን በመመልከት የተረዳችሁትን ሀሳብ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

2. ስለመጓጓዣ ምንነትና አገልግሎትየምታውቁትን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

3.እናንተ ምን አይነት የመጓጓዣ አይነቶችን ትጠቀማላችሁ?

**ተግባር አንድ፡- አዳምጦ መረዳት**

**ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

1. ካዳመጣችሁት ምንባብ የተረዳችሁትን ሀሳብ በቃል ግለፁ፡፡
2. ለመጓጓዣነት ያገለግላሉ የተባሉት ምን ምን ናቸው?
3. የየብስ መጓጓዣ ሲባል ምን ማለት ነው?
4. የባህላዊ መጓጓዣ ምንነትን ከገለፃችሁ በኋላ በምሳሌ አስረዱ፡፡

**ተግባር ሁለት፡- ቃላት**

**ከዚህ በታች በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍች በፅሁፍ ስጡ፡፡**

1. መርከብ በአንዴ ጊዜ ብዙ እቃዎችን ይጭናል፡፡
2. የየብስ መጓጓዣዎች ለማህበረሰቡ ሰፊ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡
3. ዘመናዊ መጓጓዣዎች ከባህላዊ መጓጓዣዎች ይልቅ ፈጣን ናቸው፡፡
4. መጓጓዣዎች ጭነት ከቦታ ቦታ ለማንቀሳቀስ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡
5. ከቴክኖሎጂ መስፋፋት ጋር ተያይዘው የመጡ የትራንስፖርት መገልገያዎች በርካታ ናቸው፡፡

## ክፍል ሁለት፡-መናገር

### ተግባርአንድ፡- ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

1. የባህላዊና ዘመናዊ መጓጓዣ አይነቶችን አንድነትና ልዩነት በቃል ተናገሩ።
2. መጓጓዣዎች የየብስ፣ የአየርና የውሃ ተብለው ይከፈላሉ። እያንዳንዱን ዘርዝራቸሁ ተናገሩ።
3. መጓጓዣዎች ቁሳቁስንና ሰውን ከመጓጓዝ በተጨማሪ የሚሰጡትን ጥቅም በቡድን ሆናችሁ ከተወያያችሁ በኋላ የቡድኑን ሃሳብ በአንድ ተወካይ ተማሪ ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

## ክፍል ሶስት፡- ንባብ

### የመንገድ ላይ ደህንነት



## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1.ስዕሉን ተመልክታችሁ የተረዳችሁትን ሃሳብ ለመምህራችሁ ግለፁ።

2. አንድ ሰው መንገድ ሲያቋርጥ ማድረግ ያለበትን ጥንቃቄ ተናገሩ።

3. የመንገድ ላይ ደህንነት ሲባል ምን ማለት ይመስላችኋል?

## የመንገድ ላይ ደህንነት

ከቤታችን ወጥተን ወደ የትኛውም ቦታ ስንሄድና ስንመለስ የመንገዱን ግራ ጠርዝ ይዘን መሆን አለበት። መንገድ ከማቋረጣችን በፊት በመጀመሪያ በመንገዱ ጠርዝ ላይ በመቆም የተሽከርካሪ እንቅስቃሴ እስኪቆም መጠበቅ ወይም ለማቋረጥ የሚያስችል ርቀት መኖሩን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ከመሻገራችን በፊት ግራና ቀኝ አቅጣጫን መመልከት ተገቢ ነው። በአካባቢው የእግረኛ ማቋረጫ የዜብራ ምልክት ካለ ያንን መጠቀም አለብን። ምንም እንኳን አሽከርካሪው ቢያየንም ለመሻገር መቸኮል ለአደጋ ስለሚያጋልጥ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም አሽከርካሪው ፍጥነቱን ለመቀነስና ለመቆም ጊዜ ስለሚያስፈልገው ነው።

እንዲሁም ከፍተኛ የሆነ የተሽከርካሪዎች ፍሰት ባለበት አካባቢ እንቅስቃሴ በምናደርግበት ጊዜ አሽከርካሪውም ላያዩን ስለሚችል ለራሳችን ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅብናል ። ለእግረኞች በተፈቀደ መንገድ ላይ በምንሄድበት ወቅት ለእግረኞች የወጡ ህጎችና ደንቦችን ማክበር ይኖርብናል። አለበለዚያ ለአደጋ ተጋላጭ እንሆናለን። በዚህም አደጋ ምክንያት ክቡር የሆነውን ሕይወታችንን እስከማጣት እንደርሳለን፤ ለአካል ጉዳትም

እንጋለጣለን፤ ንብረትም ሊወድም ይችላል፡፡

***አንድ ሰው መንገድ ሲያቋርጥ ምን አይነት ስህተቶችን የሚፈፅም ይመስላችኋል?***

በአጠቃላይ እግረኞች መንገድ ሲያቋርጡ ከሚፈፅሟቸው ስህተቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ ተሽከርካሪ መቆሙን ሳያረጋግጡ መሻገር፣ በተሽከርካሪ ተከልሎ መሻገር፣ለተሽከርካሪ ጀርባ ሰጥቶ መሄድ(ግራችንን ጠብቀን አለመሄድ)፣በተሽከርካሪ መንገድ ውስጥ ገብቶ መሄድ ወይም መሮጥ፤ ለእግረኞች ባልተፈቀደ መንገድ መሻገር፣ የእግረኛ መንገድ እያለ በእግረኛ መንገድ አለመጠቀም፤ትኩረትን በመንገድ ላይ ብቻ አድርጎ አለመጓዝ ፤አሽከርካሪ ይጠነቀቅልኛል ብሎ መዘናጋት፤የትራፊክ መብራትና ምልክቶችን አለማክበር እና በተሽከርካሪ መንገድ ላይ መጫወት ይገኙበታል፡፡ ስለዚህ እኛም ከላይ የተጠቀሱትን ስህተቶች ባለመፈጸም እራሳችንን ከትራፊክ አደጋ መጠበቅ ይኖርብናል፡፡

*የፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣንና ትምህርት ሚኒስቴር ካዘጋጁት ለማስተሪያነት በሚያመች መልኩ የተዘጋጀ*

## ተግባር አንድ፡- አንብቦ መረዳት

### ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ በቃል መልሱ፡፡

1. የምንባቡን ሃሳብ በዝርዝር ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
2. ሰዎች ለእግረኞች የወጣውን ህግ ባያከብሩ ምን ሊሆኑ ይችላሉ?
3. በመንገድ ላ ይ ስትንቀሳቀሱ የትኛውን መስመራችሁን ትይዛላችሁ?

4. መንገድ ስትሻገሩ የምታደርጉትን ጥንቃቄ ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

**ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆነ እውነት፣ ካልሆነ ደግሞ ሀሰት በማለት በፅሁፍ መልሱ፡፡**

1. የትራፊክ አደጋ መንስኤው የአሽከርካሪዎች ብቻ ነው፡፡
2. በተሽከርካሪ መንገድ ላይ መጫወት ለአደጋ ያጋልጣል፡፡
3. ህፃናት መንገድ ሲያቋርጡ የአዋቂዎችን እጅ ይዘው መሆን አለበት፡፡
4. አሽከርካሪው ካየን በማንኛውም ሁኔታ መንገድ ብናቋርጥ አደጋ ሊደርስብን አይችልም፡፡

## ተግባር ሁለት፡- ቃላት

**ሀ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍቻቸውን በፅሁፍ ስጡ፡፡**

1. የሚሄድበት
2. መሻገር
3. ማነጋገር
4. ማስተዋል
5. ስህተት

**ለ. ከዚህ በታች በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍቻቸውን ፃፉ፡፡**

1. የትራፊክ ህጎችን መተላለፍ <u>ለአደጋ</u> ያጋልጣል፡፡
2. ዜብራ ለእግረኛ መሸጋገሪያ ተብሎ የተሰመረ <u>ምልክት</u> ነው፡፡
3. ጠዋትና ማታ የተሽከርካሪዎች <u>ፍሰት</u> ይበዛል፡፡
4. የትራፊክ አደጋ ለህይወት <u>መቀጠፍ</u> መንስኤ ነው፡፡

5. የመንገድ ጠርዝ ላይ በመቆም ተሽከርካሪዎች እስኪያልፉ መጠበቅ አስፈላጊ ነው፡፡

**ተግባር ሶስት፡- መፃፍ**

**ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡትን ቃላት በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን በፅሁፍ መስርቱ፡፡**

1. መጫወት
2. ትኩረት
3. ሰላም
4. አደጋ
5. መሻገር
6. ተሽከርካሪ

**ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትዕዛዙን መሰረት በማድረግ በፅሁፍ መልሱ፡፡**

1. በአካባቢያችሁ በብዛት ጥቅም ላይ እየዋለ ያለው የመጓጓዣ አይነት የትኛው ነው? ለምን ?
2. የትራፊክ አደጋ እንዳይደርስባችሁ ለመከላከል የምታደርጉትን ጥንቃቄ በሶስት አረፍተ ነገሮች በመፃፍ ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡

## ክፍል አራት፡- ቃላት

### ተግባር አንድ፡- የቃላት ፍቺ

ሀ. ቀጥሎ በ "ሀ" ስር ለቀረቡት ቃላት ከ "ለ" ስር ተመሳሳይ ፍቻቸውን በመምረጥ አዛምዱ፡፡

| ሀ. | ለ. |
|---|---|
| 1. አከተመ | ሀ. ፋፋ |
| 2. ወፈረ | ለ. ተጣመረ |
| 3. ተቆራኘ | ሐ. አበቃ |
| 4. ጉልህ | መ. ረኸርም |
| 5. መለሎ | ሠ. ግልፅ |

ለ. ቀጥሎ በ "ሀ" ስር ለቀረቡት ቃላት ከ "ለ" ስር ተቃራኒ ፍቻቸውን በመምረጥ አዙምዱ፡፡

| ሀ. | ለ. |
|---|---|
| 1. መነመነ | ሀ. ውድቅት |
| 2. ቀትር | ለ. ቧልት |
| 3. ቁምነገር | ሐ. ፋፋ |
| 4. አስከፋ | መ. ታች |
| 5. ላይ | ሠ. አስደሰተ |
| 6. ቋጠረ | ረ. ፈታ |


**ሐ. ከዚህ በታች በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡**

1. ሶስና በትምህርቷ <u>አመርቂ</u> ውጤት አስመዘገበች፡፡
2. ያሲን የሶስተኛ ክፍል ተወካይ ሆኖ <u>ተመረጠ፡፡</u>
3. ለፈተና በቂ <u>ዝግጅት</u> ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
4. ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ሃብት <u>የታደለች</u> ሀገር ናት፡፡
5. ጨዋታ ስንጫወት <u>ህጎቹን</u> ማክበር አለብን፡፡

**መ. ከዚህ በታች የቀረበውን ምሳሌ መሰረት በማድረግ ቃላቱን በማጣመር አሟልታችሁ ፃፉ፡፡**

**ምሳሌ፡- ሀ.ስነ ምግባር ለ. ስነ ቃል ሐ. ስነ ዜጋ**

**መ. ስነ ጥበብ**




ምሳሌ፡-

ሀ. ቤተ መንግስት ለ.________________

ሐ.________________ መ.________________

ሠ.________________




## ክፍል አምስት፡ ፅህፈት

### ተግባር አንድ፡- መፃፍ

ሀ. ከዚህ በታች ተዘበራርቀው የተቀመጡትን ቃላት ቅደም ተከተል በማስያዝ አረፍተ ነገሮችን ፃፉ፡፡

1. አጥቦ ለበሰ ብሩክ ተኩሶ ሸሚዙን፡፡
2. ጓደኛ የሜሮን መጣች ወደ ቤት፡፡

3. ነው ስፖርት ጠቃሚ ለጤና ፡፡

4. ጎበዝ ናት ደራርቱ አትሌት፡፡

5. አልሃምዱ ነው ሰራተኛ ታታሪ፡፡

**ለ. ከዚህ በታች ተዘበራርቀው የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች በድርጊት ቅደም ተከተል አስተካክላችሁ ፃፉ፡፡**

**ምሳሌ፡-**

**ሀ. ወደ ቀጣዩ ክፍል ተዛወረ፡፡**

**ለ. ጥሩ ውጤት አመጣ፡፡**

ሐ. ዳንኤል ጠንክሮ አጠና፡፡

**ከላይ ከ ሀ እስከ ሐ የቀረቡት አረፍተ ነገሮች በቅደም ተከተል ሲፃፉ የሚከተለውን ይመስላል፡፡**

ዳንኤል ጠንክሮ አጠና፡፡

ጥሩ ውጤት አመጣ፡፡

ወደ ቀጣዩ ክፍል ተዛወረ፡፡

1. አንደኛ ክፍል ገባች፡፡
2. በርትታ አጠናች፡፡
3. ኤልዳና ሰባት አመት ሞላት፡፡
4. ከክፍል አንደኛ ወጣች፡፡

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

### ተግባር አንድ፡- ገላጮችን መለየት

ማስታወሻ

ገላጮች ከስም በፊት ወይም በኋላ በመግባት ስምን ይገልፃሉ፡፡

ምሳሌ፡- ትልቅ፣ ትንሽ፣ ቀይ፣ ሰማያዊ፣ ሞላላ፣ አረንጓዴ ወዘተ. የስም ገላጮች ናቸው፡፡

ሀ. ከዚህ በታች በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ገላጮች በምሳሌው መሰረት ለይታችሁ አስምሩባቸው፡፡

**ምሳሌ፡-**

ሀ. እኔ <u>ቀይ</u> ሹራብ አለኝ፡፡

ለ. ሳምሶን <u>ጎበዝ</u> ተማሪ ነው፡፡

1. ረባሹ ልጅ ተቀጣ፡፡
2. ሀና ትልቅ ዳቦ ደፋች፡፡
3. ሀይሌ ድንቅ አትሌት ነው፡፡
4. ትንሽ ድመት አየሁ፡፡
5. ሙባረክ ጥሩ መፅሐፍ ገዛ፡፡

ለ. ከዚህ በታች በቀረቡት ገላጮች አረፍተ ነገሮችን በፅሁፍ መስርቱ፡፡

1. አረንጓዴ
2. ሰነፍ
3. ትልቅ
4. አሮጌ
5. ወፍራም

## የክለሳ ጥያቄዎች

**ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትዕዛዙን መሰረት በማድረግ መልስ ስጡ፡፡**

1. መጓጓዣ ባይኖር የሰው ልጅ ሊገጥመው የሚችለውን ችግር ወላጆቻችሁን ወይም የምታውቁትን ሰው ጠይቃችሁ በመምጣት ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

2. የመንገድ ላይ ደህንነት ሲባል ምን ማለት ነው? የሳይንስ መምህራችሁን ጠይቃችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በፅሁፍ አቅርቡ፡፡

3. ከዚህ በታች በቀረቡት ገላጮች አረፍተ ነገር መስርቱባቸው፡፡

ሀ. ቀጭን

ለ . ፈጣን

ሐ. ጣፋጭ

3. ከዚህ በታች ተዘበራርቀው የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች በድርጊት ቅደም ተከተል አስተካክላችሁ ፃፉ፡፡

ሀ. በሚገባ ደጋግማ አጠበች

ለ. ገነት ቡና ገዛች፡፡

ሐ. በማሽን ፈጨች፡፡

መ. አፍልታ ከእናቷ ጋር ጠጣች፡፡

ሠ. በጥንቃቄ ቆላች፡፡

5. ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ፃፉ፡፡

ሀ.ማወዳደር

ለ.ተኮፈሰ

ሐ.አስተዋጽኦ

# ምዕራፍ ስድስት

## ስነ ምግባር

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ካዳመጣችሁት ምንባብ ውስጥ ጠቃሚ ነጥቦችን ትናገራላችሁ፡፡
- ካነበባችሁት ምንባብ ውስጥ ጥሩና መጥፎ ስነ ምግባሮችን ትለያላችሁ፡፡
- ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ ተጠቅማችሁ አረፍተ ነገር ትመሰርታላችሁ፡፡
- ለቃላፍት ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

አቶ አየለና አታላዩ ሰውዬ



## ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ስዕሉን በመመልከት የተረዳችሁትን መልዕክት ለመምህራችሁ በቃል ተናገሩ፡፡
2. ‹‹አቶ አየለና አታላዩ ሰውዬ›› ከሚለው ርዕስ በመነሳት ስለምን የምታዳምጡ ይመስላችኋል?

3.አንድ ሰው ታማኝ ነው የሚባለው ምን ሲያደርግ ይመስላችኋል?

## ተግባር አንድ፡- አዳምጦ መረዳት

**ሀ. ባዳመጣችሁትምንባብ መሰረት ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡**

1. ያዳመጣችሁትን ምንባብ ዋና ሃሳብ በቃል ተናገሩ፡፡
2. አቶ አየለ አታላዩን ሰውዬ ያገኘው የት ነው?
3. አታላዩ ሰው ወደ አቶ አየለ ቤት መሄዱ የፈለገው ለምንድን ነው?

4.በመንገድ ዳር ተኝተው እርዳታን የሚጠይቁ ሰዎች ሁሉ አታላይ ናቸው ብላችሁ ታምናላችሁ? ለምን?

**ለ. ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሰረት በማድረግ ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በፅሁፍ መልሱ፡፡**

1. አቶ አየለ ባታላዩ ሰው የተታለለው ለምንድን ነው?
2. እናንተ አቶ አየለን ብትሆኑ ምን ታደርጉ ነበር?
3. አታላዩ ሰውዬ በአቶ አየለ ንግግር ልቡ የተነካው ለምንድን ነው?
4. ታማኝነት ያለውን ጠቀሜታ ቤተሰቦቻችሁን ጠይቃችሁ በመምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡላቸው፡፡

## ክፍል ሁለት፡- ንባብ

### ሮዛና ሳሙኤል



### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ስዕሉን በመመልከት የተረዳችሁትን ሃሳብ ለመምህራችሁ በቃል ተናገሩ፡፡
2. ስነ ምግባር ሲባል ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? የምታውቁትን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

### ሮዛና ሳሙኤል

ሮዛና ሳሙኤል የአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ አንድ ቀን እያጠኑ እያለ እስካሁን ያነበብነውን አንዳችን ለአንዳችን ተራ በተራ እናስረዳ በማለት ተወያዩ፡፡ ከዚያም ሮዛ በመልካም ስነ ምግባር ላይ እንድታቀርብ ሣሙኤል ደግሞ መጥፎ ስነምግባር ላይ እንዲያቀርብ ተስማሙ፡፡ ሃሳባቸውንም እንደሚከተለው

በመጠያየቅ ጀመሩ፡፡ መልካም ስነ ምግባርን አስመልክቶ የመጀመሪያው ጠያቂ ሳሙኤል ነበር፡፡

**ሳሙኤል፦** ‹‹መልካም ስነ ምግባር ማለት ምን ማለት ነው?››

**ሮዛ፦** ‹‹መልካም ስነ ምግባር ማለት መልካም ፀባይ ወይም ባህሪ ያለው ሰው ነው፡፡ ህብረተሰባችን የሚወደውና የሚቀበለው ማንኛውም ዓ ይነት መልካም ተግባር ነው፡፡››

**ሳሙኤል፦** ‹‹ለመሆኑ አንድ ሰው መልካም ስነ ምግባር እንዳለው በምን ይታወቃል?››

**ሮዛ፦** ‹‹መልካም ስነ ምግባር ያለው ሰው ትላልቅ ሰዎችን ያከብራል፤ አቅመ ደካሞችን ይረዳል፤ ስራውን በአግባቡ ይሰራል፤ አካባቢውን ይንከባከባል፤ አይዋሽም፤ አያታልልም፤ አያጭበረብርም፤ ከሰዎች ጋር አይጣላም፤ ጊዜውን በአግባቡ ይጠቀማል፡፡ መልካም ስነምግባር ያለው ሰው ሀገሩን ይወዳል፤ የተቸገረን ይረዳል፡፡››

**ስለ መጥፎ ስነ ምግባር ምን ምን ጉዳዮችን የሚያነሱ ይመስላችኋል?**

**ሮዛ፦** ‹‹ጥያቄህን ጨርሰህ ከሆነ እኔ ልቀጥል፡፡›

**ሳሙኤል፦** ‹‹አዎ አሁን አንቺ ጠይቂኝ፡፡››

**ሮዛ፦** ‹‹መጥፎ ስነ ምግባር ምንድን ነው?››

**ሳሙኤል፦** ‹‹መጥፎ ስነ ምግባር መጥፎ ተግባር ሲሆን ህብረተሰባችን የማይወደውና የማይቀበለው ነው፡፡››

**ሮዛ፦** ‹‹መጥፎ ስነ ምግባር ያለው ሰው እንዴት ይታወቃል?››

**ሳሙኤል፦** ‹‹መጥፎ ስነ ምግባር ያለው ሰው ከሰዎች ጋር አይስማማም፤ በሆነው ባልሆነው ይጣላል፤ ወላጆቹንም ሆነ

ሌሎች ሰዎችን አያከብርም፤ ደካሞችን ይንቃል፤ ጊዜውን በአግባቡ አይጠቀምም፤ አታላይና አጭበርባሪ ነው፤ ይዋሻል፤ ሀላፊነቱን በአግባቡ አይወጣም። እንደዚህ አይነት ባህሪ ያላቸውን ሰዎች ሰው አይወዳቸውም።››

**ሮዛ፡-** ‹‹መልካም ስነ ምግባርን ማን ሊያስተምር ይችላል?››

**ሳሙኤል፡-** ‹‹ወላጆችና ትምህርት ቤቶች ናቸው። ወላጆች ልጆቻቸውን መልካም ስነ ምግባር እንዲኖራቸው በስነ ስርዓት ኮትኩተው ማሳደግ ይኖርባቸዋል። ትምህርት ቤቶችም ጥሩ ትውልድ ለማፍራት መልካም ስነ ምግባርን በማስተማር ትልቅ አስተዋፅኦ ማድረግ አለባቸው።››

**ሮዛ፡-**‹‹ጥያቄዎቼን ጨርሻለሁ አንተ ምትጨምረው አለ?››

**ሳሙኤል፡-** ‹‹እኔም ጨርሻለሁ ። ለዛሬ እስካሁን የተወያየነው ይበቃናል አሁን ትንሽ ማረፍ ይኖርብናል››

**ሮዛ ፡-** ‹‹እውነት ብለሃል እኔም ስለደከመኝ ማረፍ እፈልጋለሁ። መልካም የእረፍት ጊዜ ጓደኛዬ።››

**ሳሙኤል፡-** ‹‹ላንቺም መልካም እረፍት››

## ተግባር አንድ፡- አንብቦ መረዳት

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ በቃል መልሱ።**

1. ምንባቡ ውስጥ የተጠቀሱት ባለታሪኮች እነማን ናቸው?
2. መልካም ስነ ምግባር ማለት ምን ማለት ነው?
3. አንድ ተማሪ ጥሩ ስነ ምግባር እንዲኖረው ምን ማድረግ

አለበት?

4. አንድ ሰው መጥፎ ስነ ምግባር አለው የሚያስብሉት ባህሪያት ምን ምን ናቸው?

## ተግባር ሁለት፡- ቃላት

**ሀ. ቀጥሎ በ "ሀ" ስር ለቀረቡት ቃላት ከ "ለ" ስር ተመሳሳይ ፍቻቸውን በመምረጥ አዛምዱ፡፡**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ተወያዩ | ሀ. ሚና |
| 2. ፀባይ | ለ. ተመካከሩ |
| 3. ይረዳል | ሐ. ባህሪ |
| 4. አስተዋፅኦ | መ. አበቃ |
| 5. ጨረሰ | ሠ. ያግዛል |

**ለ. የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች ቀጥሎ በተሰጡት ቃላት አሟልታችሁ ፃፉ፡፡**

| | | |
|---|---|---|
| ስነ ምግባር | ትውልድ | ማገገዝ |
| አይዋሽም | ኃላፊነት | ይንከባከባል |

1. የእኛ__________የራሱን አሻራ ማሳረፍ አለበት፡፡

2. መልካም ዜጋ____________ይሰማዋል፡፡

3. ልጆች ከህፃንነታቸው ጀምሮ መልካም_________መማር አለባቸው፡፡

4.መልካም ስነ ምግባር ያለው ሰው የተፈጥሮ ሃብቶችን_____፡፡

5.በዙሪያችን ያሉ አቅመ ደካሞችን________የሁላችንም ግዴታ ነው፡፡

## ተግባር ሶስት፡- መፃፍ

**ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ በፅሁፍ መልሱ፡፡**

1. ከምንባቡ የተረዳችሁትን ሀሳብ በሶስት አረፍተ ነገሮች ግለፁ፡፡
2. መልካም ስነ ምግባር የሚጠቅመው ማንን ነው? ለምን?
3. መጥፎ ስነ ምግባር የሚጎዳው ማንን ነው? ለምን?

# ክፍል ሶስት፡- ቃላት

## ተግባር አንድ፡- የቃላት ፍቺ

**ሀ. ቀጥሎ በ"ሀ" ስር ለቀረቡት ቃላት ከ "ለ" ስር ተቃራኒ ፍቻቸውን በመምረጥ አዛምዱ፡፡**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. አሞካሸ | ሀ. ፅድቅ |
| 2. ተነታረከ | ለ. አበላሸ |
| 3. አሳመረ | ሐ. ገለጠ |
| 4. ጋረደ | መ. ተስማማ |
| 5. ኩነኔ | ሠ. አጥላላ |

**ለ. ለሚከተሉት ቃላት ከሳጥኑ ውስጥ ተስማሚ የሆኑ ተጣማሪ ቃላትን በመምረጥ አጣምሩ፡፡**

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሳጥን | አበር | ደንብ | ሰፊ | ተከተል | ቀር | ቀደም |

**ምሳሌ፡- ኋላ ቀር**

1. ኋላ
2. ቁም
3. ግንባር
4. ቅደም
5. ግብሬ
6. ህገ
7. ልብስ

## ክፍል አራት፡-ፅህፈት

### ተግባር አንድ፡- መፃፍ

**ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡትን አረፍተ ነገሮች ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ በመጠቀም አሟልታችሁ ፃፉ፡፡**

| አራት ነጥብ (፡፡) | ጥያቄ ምልክት (?) | ቃለ አጋኖ (!) | ትዕምርተ ጥቅስ (‹‹ ››) | ሁለት ነጥብ (፡) | ነጠላ ሰረዝ (፣) |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |

1. የፈተናው ቀን መቼ ነው
2. ሰውን ሰው ያደረገው ስራ ነው አለች አያቴ
3. ግብርና የሀገራችን ኢኮኖሚ ዋልታ ነው
4. ጎሽ ስራ ፈጣሪ በመሆኑ ተሸለመ
5. ጠዋት ትምህርት የሚጀመረው 2፡30 ነው

**ለ. በሳጥኑ ውስጥ ያሉትን ስርአተ ነጥቦች በመጠቀም ከታች በቀረቡት ቃላት አረፍተ ነገር መስርቱ፡፡**

| ‹‹ ›› | ፡፡ | ፣ | ! | ? | ፡ |
|---|---|---|---|---|---|

1. መፍትሔ
2. አባይ
3. ቆጠበ
4. ትዕግስት
5. ይቅርታ

## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

### ተግባር አንድ፡- ተውሳከ ግስ

ማስታወሻ

ተውሳከ ግስ በሌላ ስሙ የግስ ገላጭ ተብሎ የሚጠራ ነው። ተውሳከ ግስ ከግስ በፊት በመግባት ስለግሱ ተጨማሪ መረጃ የሚሰጥ ቃል ነው።

**ምሳሌ፡- ክፉኛ፣ ቶሎ፣ ምንኛ፣ ገና፣ መቼ፣ እንዴት የመሳሰሉት ተውሳከ ግስ ናቸው።**
**በአረፍተ ነገር ውስጥ ሲገቡ ደግሞ የሚከተለውን ይመስላል።**
**ሀ. አቤሴሎም ቶሎ መጣ።**
**ለ. ልጁ እግሩን ክፉኛ ታሟል።**

**ከዚህ በታች በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚገኙ ተውሳከ ግስ ቃላትን በማስመር ለዩ።**

1. መምህራችን መቼ መጡ?
2. ታክሲው ገና አልደረሰም።
3. ቃለአብ ከእንቅልፉ ቶሎ ነቃ።
4. የወላጆች በዓል ነገ ይከበራል።
5. እንዴት መጣህ?

## የክለሳ ጥያቄዎች

**ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትዕዛዙን መሰረት በማድረግ መልስ ስጡ፡፡**

1. ስለ መልካምና መጥፎ ስነ ምግባር በሬዲዮ ወይም በቴሌቭዥን የሚተላለፉ መልዕክቶችን አዳምጣችሁ በመምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል ተርኩላቸው፡፡

2. ስለመልካም ስነ-ምግባር የሚተርኩ ተረቶችን ፈልጋችሁ በማንበብ ፍሬ ሀሳቡን ፅፋችሁ በመምጣት ለመምህራችሁ አንብቡላቸው፡፡

3. ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን ስጡ፡፡

   ሀ. ውድ

   ለ. ቅርብ

   ሐ. ማስረዘም

4. የሚከተሉትን ስርዓተ ነጥቦች በመጠቀም አረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

   ሀ. አራት ነጥብ (፡፡)

   **ለ.** ጥያቄ ምልክት (?)

   ሐ. ትዕምርተ ጥቅስ (‹‹ ››)

6. ከዚህ በታች በቀረቡት የቃላት ዝርዝር ውስጥ ተውሳከ ግስ የሆኑ ቃላትን ለይታችሁ ፃፉ፡፡

   ሀ. አበበ፣ ገና፣ ሄደ፣ ምንኛ፣ ቢጫ፣ ትምህርት ቤት

   ለ. ክፉኛ፣ ሬዲዮ፣ ቶሎ፣ መቀሌ፣ መቼ

# ምእራፍ ሰባት

## ግብርና

### የሚጠበቅ ውጤት

ከዚህ ምእራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሰረት በማድረግ የሚና ጨዋታ ትጫወታላችሁ፡፡
- ካነበባችሁት አንቀፅ ውስጥ ዋናውን ሀሳብ ትፅፋላችሁ፡፡
- ያነበባችሁት ምንባብ ውስጥ ያገኛችሁትን ዋና ጉዳይ ትፅፋላችሁ፡፡
- ለአዳዲስ ቃላት ትርጉም ትሰጣላችሁ፡፡
- በፅሁፍ ውስጥ ተውሳከ ግሶችን ትለያላችሁ



## ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ስእሉን ስትመለከቱ ስለምን የምታዳምጡ ይመስላችኋል፡፡
2. ‹‹ ግብርና›› ሲባል ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?
3. የጓሮ አትክልት ሲባል ምን ማለት ነው?

## ተግባር አንድ፡- አዳምጦ መረዳት

**ሀ**. ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሰረት በማድረግ ለሚከተለት ጥያቄዎች መልሳችሁን በቃል ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

1. በከተማ ግብርና ውስጥ ሊከናወኑ የሚችሉ ተግባራት ምን ምን ናቸው?
2. የምንባቡን አጠቃላይ ሃሳብ አሳጥራችሁ በቃላችሁ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

7. በግብርና ላይ ለመሰማራት የባለሙያ ምክር ለምን ያስፈልጋል?
8. አንድ የከተማ ኗሪ ከግብርና ዘርፍ የሚያገኘው ጠቀሜታ ምንድን ነው?

**ለ**. ከዚህ በታች ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ለጥያቄዎቹ በፅሁፍ መልስ ስጡ፡፡

1. እናንተ በምትኖሩበት ግቢ ውስጥ የጓሮ አትክልቶችን ትተክላላችሁ? መልሳችሁን በምክንያት በማስደገፍ ፅፋችሁ አቅርቡ፡፡
2. በግብርና በመሰማራት እንዴት የምግብ ፍጆታችንን ገቢያችንን ማሳደግ እንችላለን? ቤተሳበችሁን ጠይቃችሁ ፅፋችሁ በመምጣት ለክፍሉ ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

3. ለምግብነት የምትጠቀሙባቸውን አትክልቶች የምታገኙት ከየት ነው? ወላጆቻችሁን ጠይቃችሁ ፅፋችሁ በመምጣት ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።

**ተግባር ሁለት፡- ቃላት**

**ሀ. ለሚከተሉት አዳዲስ ቃላት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ከሰንጠረዡ እየመረጣችሁ አዛምዱ።**

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሰብል | ድርሻ | ማሳ | ዘዴ | ማረስረስ | ምርታማ | የውሃ ማስተላለፊያ | ማጠራቀም |

1. ውጤታማ
2. ማርጠብ
3. የእርሻ ቦታ
4. መሰብሰብ
5. ብልሃት
6. ፋንታ
7. ቦይ
8. አዝመራ

**ለ. ከዚህ በታች የቀረቡትን ቃላት በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን መስርቱ።**

1. ምርጥ ዘር

2. ፍጆታ

3. እሸት

4. መስኖ

5. ዘመናዊ

## ክፍል አንድ፡-ንግግር

### ተግባር አንድ፡- መናገር

**ከዚህ በታች የቀረበላችሁን ጭውውት መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት ጥንድ ጥንድ በመሆን የሚና ጨዋታውን ተግብሩ፡፡**

**ለምሳሌ፡-**

**ምህረት**፡-አህመድ እኔ በትርፍ ጊዜዬ የጓሮ አትክልቶችን አለማለሁ፡፡ አንተስ?

**አህመድ**፡-አምስት እንቁላል ጣይ ድሮዎች አሉኝ፡፡ እነሱን እንከባከባለሁ፡፡ ለመሆኑ አንቺ ምን ምን የጓሮ አትክልቶችን ታለሚያለሽ?

**ምህረት**፡- በአብዛኛው በትንሽ ቦታ ላይ የሚለሙ አትክልቶች ናቸው፡፡ እንደ ቆስጣ፣ ሰላጣ፤ ቲማቲምና ቃሪያ አለማለሁ፡፡ በእረፍት ጊዜዬ አትክልቶችን በመንከባከብ በማሳለፌ ደስተኛ ነኝ፡፡

**አህመድ**፡- እኔም በእረፍት ጊዜዬ ከዶሮዎቼ ጋር ነው የማሳልፈው፡፡ ምግብ አዘጋጅላቸዋለሁ፡፡ ለተለያየ በሽታ እንዳይጋለጡ ቤታቸውን አፀዳለሁ፡፡ እንቁላል መጣያ ቦታቸውንም አመቻቻለሁ፡፡

## ክፍል ሁለት፡- ንባብ

### አይበገሬዎቹ እህትማማቾች



## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ስዕሉን በመመልከት የተረዳችሁትን ሀሳብ ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡

2. በአካባቢያችሁ ሰዎች በአብዛኛው የሚሰማሩባቸው የስራ አይነቶች ምንድን ናቸው?

3.‹‹አይበገሬዎቹ እህትማማቾች›› የሚለው ምንባብ ስለምን የሚተርክ ይመስላችኋል?

### አይበገሬዎቹ እህትማማቾች

በአርባ ምንጭ ከተማ አቅራቢያ የሚኖሩ ሶስት እህትማማቾች ነበሩ፡፡ ጎበዝና ታታሪ ወጣቶች ቢሆኑም ስራ ግን አልነበራቸውም፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ‹‹መፍትሄ መፈለግ አለብን ያለስራ እስከመቼ እንደዚህ እንኖራለን›› በማለት ተመካከሩ፡፡‹‹መማራችን አንድም የሚጠቅመን ለችግሮቻችን አስበን መፍትሔ ለመለፈለግ ነው፡፡

ስለዚህ አንድ ብልሃት መፈለግ አለብን›› ተባባሉ፡፡ ከዚያም ‹‹‹የእናትና አባታችን መሬት አይደለምን? እዚያ ላይ አንሰራም? መሬቱም ጦም ማደር የለበትም›› በማለት ተስማሙ፡፡ የእናትና አባታቸውን መሬት በማረስ ለመጠቀም ወሰኑ፡፡ ይሁን እንጂ ለእርሻ ስራው የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች አልነበሯቸውም፡፡

"ለእርሻ ስራው የሚያስፈልጉንን ቁሳቁሶች እንደምንም ብለን ፈልገን ስራውን መጀመር አለብን" ሲሉ ተወያዩ፡፡ ከዚያም አንድ ቀን በአካባቢው ወደ ሚኖረው አጎታቸው ጋር ሄደው የሚያስፈልጋቸውን የእርሻ መሳሪያ እንዲሰጣቸው ጠየቁ፡፡ አጎታቸውም በሃሳባቸው ተስማምቶ የሚያስፈልጓቸውን የእርሻ መሳሪያዎች አሟሉላቸው፡፡ እህትማማቾቹም በተሰጣቸው የእርሻ መሳሪያ በመታገዝ ማሳውን አርሰው ጨረሱ፡፡ መሬቱን አርሰው ከጨረሱ በኋላ እህሉን ለመዝራት መሬቱን በውሃ ማረስረስ ነበረባቸው፡፡ ቀኑን ሙሉ በጀሪካን እየቀዱ ማሳው ላይ ቢረጩትም የሚፈልጉትን ያህል አልራሰም፡፡ ‹‹እስቲ አንድ መፍትሄ አስቡ›› አለች ትንሿ እህታቸው፡፡ ‹‹ወንዙ ቅርብ ቢሆንም እንደዚህ እየቀዳን ማጠጣት በጣም አስቸጋሪ ነው አለች›› ከዚያም አንድ መፍትሄ ላይ ደረሱ፡፡

## እህትማማቾቹ ምን አይነት መፍትሄን የሚያመጡ ይመስላችኋል ?

የውሃ ማስተላለፊያ የፕላስቲክ ቱቦ ገዝተው በመጠቀም ከወንዝ ወደማሳው ውሃ ማፍሰስ ጀመሩ፡፡ በማሳቸው ላይ የተለያዩ የአዝርእት አይነቶችን በመዝራት እንክብካቤ ያድርጉላቸው ጀመር፡፡ ማሳው ላይ ከዘሩት የእህል አይነቶችም አንዱ በቆሎ ሲሆን የአፈሩ ለምነትና

የሚያደረጉት እንክብካቤ ስለተመቸው ፍሬያማ ሆነ፡፡ አባታቸው ግን ሴት ልጅ የእርሻ ስራ ላይ ስትሰማራ የተለመደ ባለመሆኑ ተግባራቸውን ይቃወማቸው ነበር፡፡ ሌሎች የመንደሩ ሰዎች ደግሞ ልክ እንደ አባታቸው ሁሉ የሴት ያልሆነን ስራ የሚሰሩ ባለጌዎች እያሉ ይነቅፏቸውና ይጠሏቸው ነበር፡፡ሶስቱም እህትማማቾች የመጀመሪያውን እሸት ቆርጠው ለእናትና አባታቸው አቀረቡ፡፡ አባታቸው እስከዛሬ በሴትነታቸው ስለአንኳሰሳቸው በጣም አፈረ፡፡ ‹‹ልጆቼ በጣም ተሳስቼ በድያችኋለሁና ይቅርታ አድርጉልኝ›› ብሎ ጠየቃቸው፡፡

እህትማማቾቹ ግን የአባታቸውን ጉልበት እየሳሙ ‹‹አባባ ምንም ብትሆን ስላስተማርከን ብቻ ባለውለታችን ነህ፡፡ በመማራችን ደግሞ መለኛና ታታሪ ሆንን›› አሉት፡፡ የመንደሩ ሰዎችም ተሰብስበው መጥተው ይቅርታ ጠየቋቸው፡፡ እህል ሲደርስም በመሰብሰብ አገዟቸው፡፡ የተሰበሰበውንም እህል ገበያ ወስደው በመሸጥ ብራቸውን ባንክ ሄደው የቁጠባ ሂሳብ በመክፈት ግማሹን ባንክ አስገቡ፡፡ የቀረውን ለሚፈልጉት ተግባራት አዋሉት፡፡

**ምንጭ፡-** ዳንኤል ወርቁ (2011 ዒ.ም) የተማሩት እህትማማቾች፣ ተሻሽሎ የተወሰደ

## ተግባር አንድ፡- አንብቦ መረዳት

### ሀ. ለሚከተሉት ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች መልሳችሁን በቃል ተናገሩ፡፡

1. ከምንባቡ የተረዳችሁትን ሀሳብ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
2. በምንባቡ ውስጥ ጦም ማደር የለበትም የተባለው ምንድን ነው?

3. እህትማማቾቹ ለእርሻ ስራ የሚያስፈልጋቸውን ቁሳቁስ ያገኙት ከየት ነው?

4. አንድ ሰው ችግር ሲያጋጥመው ምን ማድረግ አለበት?

**ለ. ምንባቡን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን እውነት፣ ስህተት የሆነውን ደግሞ ሀሰት በማለት በፅሁፍ መልሱ:: ምክንያታችሁንም በፅሁፍ አስፍሩ::**

1. መማር የችግር መፍቻ ቁልፍ ነገር ነው::
2. ስራ መፍጠር የእያንዳንዱ ሰው ሀላፊነት ነው::
3. እህትማማቾቹ ውሃውን በጀሪካን እየተሸከሙ ማረስረስ አልቻሉም::
4. እህትማማቾቹ በመጀመሪያ እሸቱን ያቀመሱት ለጎረቤቶቻቸው ነው::
5. ሶስቱ ሴቶች በሚኖሩበት አካበባቢ ሴት ልጅ ስታርስ ማየት የተለመደ አልነበረም::

**ሐ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በፅሁፍ መልስ ስጡ::**

1. ቀደም ብሎ የቀረበውን ምንባብ እንደገና አንብቡና የመጀመሪያውን አንቀፅ ዋና ሀሳብ በራሳችሁ አገላለጽ አሳጥራችሁ ፃፉ::
2. ሴቶች የሚሳተፉባቸው የግብርና ስራዎች ምን ምን እንደሆኑ ቤተሰቦቻችሁን በመጠየቅ ፅፋችሁ በመምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው::

ተግባር ሁለት፡- አቀላጥፎ ማንበብ

**ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ ትእዛዝ መሰረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ::**

**ደንና ህይወት**

በድሮ ጊዜ አእዋፋትና እንስሳት በጋራ የሚኖሩበት ሰፊ ደን ነበር:: ይህ በልምላሜው የሚታወቅና ለምግብ የሚሆኑ ልዩ ልዩ

ፍራፍሬዎች የሞሉበት ስለነበር የተለያዩ እንስሳትና አእዋፍ መኖሪያ ነበር። ይሁን እንጅ በአካባቢው የሰው ልጆች ከሰፈሩበት ጊዜ አንስቶ ዛፎች ክፉኛ እየተጨፈጨፉና እየተመነጠሩ አለቁ። በአካባቢውም ዝናብ ጠፋ። በአቅራቢያው የነበሩት ወንዞችና ምንጮችም እያደር እየቀነሱና እየደረቁ ሄዱ። መሬትም ተራቆተች። በዚህ ምክንያት ደን ቀስ በቀስ እየተመናመነ ሄደ። በውስጡ የነበሩት እንስሳትም ምግብ የሚሆናቸውን ፍራፍሬና ስራስሮች ለማግኘት እየተሳናቸው መጣ። ብዙም ሳይቆይ በአካባቢው ረሀብና ቸነፈር ተከሰተ። በዚያ ይኖሩ የነበሩት አዕዋፍና እንስሳት በሁኔታው ተደናገጡ። ከነበሩት ጥቂት ዛፎች የተረፉትን ፍራፍሬዎች በጋራና በቁጠባ በመቅመስ ትንሽ ወራትን አብረው አሳለፉ። ችግሩ እየበረታ ሲመጣ ጦም ውለው ማደር ጀመሩ። በዚህ የተነሳ በደኑ ውስጥ ይኖሩ የነበሩት እንስሳትና አእዋፍ ችግራቸውን ለመፍታት ምን ማድረግ እንዳለባቸው ተወያዩ።

ምንጭ፡- ውዳላት ገዳሙ (ብድሯን ያልከፈች ወፍ) ተሻሽሎ የተወሰደ

## ተግባር ሶስት፡- ቃላት

**ከዚህ በታች በቀረበት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍች ፃፉ።**

1. ያለስራ <u>እስከመቼ</u> እንደዚህ እንኖራለን።
2. እንስሳትና አእዋፍ ደኖች ሲጠፉ መኖር <u>ተሳናቸው</u>።
3. በደኖች መመንጠር ምክንያት ከፍተኛ የሆነ ድርቅ <u>ተከሰተ</u>።
4. ሰፊው ደን ሙሉ በሙሉ በመውደሙ ከፍተኛ <u>ቸነፈር</u> ተከሰተ።
5. አጎታቸው ለእህትማማቾች የእርሻ መሳሪያ በመስጠት <u>አገዟቸው</u>።

6. በአካባቢያችን የወዳደቁ ቁሳቁሶችን በመጠቀም የውሃ መሳቢያ መስራት ይቻላል፡፡

**ተግባር አራት፡- መፃፍ**

**በአካባቢያችሁ በብዛት የሚመረቱ የአትክልት አይነቶችን ፅፋችሁ በመምጣት ለመምህራችሁ አንብቡላቸው፡፡**

## ክፍል ሶስት፡- ቃላት

**ተግባር አንድ፡- የቃላት ፍች**

ሀ. በ "ሀ" ረድፍ ላሉት ቃላት ከ "ለ" ረድፍ ተመሳሳይ ፍች በመምረጥ አዛምዱ፡፡

| ሀ. | ለ |
|---|---|
| 1. የሚመነጭ | ሀ. እጅ ሰጠ |
| 2. ተማረከ | ለ. ጫካ |
| 3. ቋጨ | ሐ. የሚነሳ |
| 4. ያላሰለሰ | መ. ዋና ከተማ |
| 5. ደን | ሠ. ጨረሰ |
| 6. መዲና | ረ. ሰጠ |
| 7. ለገሰ | ሰ. የማያቋርጥ |

ለ. በ "ሀ" ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ከ "ለ" ረድፍ ተቃራኒ ፍች በመምረጥ አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ብስል | ሀ. ሽቅብ |
| 2. ቁልቁል | ለ. መዳከም |

3. መበርታት ሐ. ጥሬ

4. ወራጅ መ. ተደፈነ

5. ተሸነቆረ ሠ. ወጭ

**ሐ. በሚከተሉት ቃላት ላይ የተጨመሩትን ቅጥያዎች ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ለይታችሁ አስምሩ።**

**ምሳሌ፡-** <u>**እየ-**</u>ሄዱ፣ <u>አስ-</u>ተማሪ

1. እየጻፉ 2. በሬዎች 3. ሄደች 4. ሲበሉ 5. ከመጣ

**መ. በሚከተሉት ቃላት ላይ የተጨመሩትን ቅጥያዎች ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ለይታችሁ አውጡ።**

**ምሳሌ፡-** ወንዶች (-ኦች)

1. ወረቀቶች
2. ተማሪዎች
3. ሰራች
4. ቤቶች
5. ተመገበች

## ክፍል አራት፡- ሰዋስው

### ተግባር አንድ፡- ተውሳከ ግስ

**ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡትን አረፍተ ነገሮች ምሳሌውን መሰረት በማድረግ የስም ገላጭ፣ ስም፣ የግስ ገላጭና ግስ በማለት ለይታችሁ ፃፉ።**

| ተ.ቁ | አረፍተ ነገር | የስም ገላጭ | ስም | የግስ ገላጭ | ግስ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ችኩል ሰው ተረጋግቶ አይሰራም። | ችኩል | ሰው | ተረጋግቶ | አይሰራም |
| 2 | ታታሪው ነጋዴ ከሀላባ መጣ። | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 3 | አዱሱ ልብስ በጣም ያምራል። | | | | |
| 4 | ጀግናው ወታደር በድል ተመለሰ። | | | | |
| 5 | ረጅሙ ሰው እየሮጠ ሄደ። | | | | |
| 6 | ስስ ወረቀት ቶሎ ይቀደዳል። | | | | |

ሀ. በ "ሀ" ምድብ የቀረቡትን ቃላት ከ "ለ" ምድብ ከቃል ክፍላቸው ጋር አዛምዱ።

<u>ሀ</u> <u>ለ</u>

1. ሶዶ ሀ. የስም ገላጭ

2. ቀጭን ለ.ተውሳከ ግስ

3. ወደቀ ሐ. ግስ

4. ቶሎ መ. ስም

ለ. ከዚህ በታች የቀረቡትን የግስ ገላጮች በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን መስርቱ።

1. ከየት
2. በፍጥነት
3. እየሮጠ
4. ምንኛ
5. እንዴት

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. አንድ ስለገበሬና ነጋዴ የሚያወራ ተረት ፈልጋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡
2. ‹‹አይበገሬዎቹ እህትማማቾች›› የሚለውን ምንባብ በግላችሁ አንድ ጊዜ ደግማችሁ በማንበብ በእያንዳንዱ አንቀፅ ውስጥ ያሉትን ዋና ዋና ሀሳቦች በአራት አረፍተ ነገሮች አሳጥራችሁ ፃፉ፡፡
3. ‹‹ደንና ህይወት›› ከሚለው ምንባብ ውስጥ ፍሬ ሀሳቡን በአንድ አረፍተ ነገር አሳጥራችሁ ፃፉ፡፡
4. ቀጥሎ በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን የግስ ገላጮች ለይታችሁ ፃፉ፡፡

    ሀ. ያስሜን ወደ ወልቂጤ ሄደች፡፡

    ለ. አብርሃም ስለታመመ አልመጣም፡፡

    ሐ. የአማርኛ ፈተና ነገ ይሰጣል፡፡

5. ለሚከተሉት ተመሳሳይ ፍች ስጡ፡፡

    ሀ. ሀሴት

    ለ. ለኮሰ

    ሐ. አለኝታ

# ምእራፍ ስምንት

# ስራ

ከዚህ ምእራፉ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ባዳመጣችሁት ምንባብ ውስጥ የተነሱ ጉዳዮች ላይ ልምምድ ታደርጋላችሁ፡፡
- ምንባቡን አንባባችሁ መልእክቱን ትረዳላችሁ፡፡
- የወደፊት እቅዳችሁን ትፅፋላችሁ፡፡
- ለአዳዲስ ቃላት ፍች ትሰጣላችሁ፡፡
- ተያያዥነት ያላቸውን አረፍተ ነገሮች ትመሰርታላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡— ማዳመጥና መናገር

### ታታሪው ሰራተኛ



## የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

**ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች**

1. ጥንድ ጥንድ በመሆን ስእሉን ተመልከቱና የተረዳችሁትን ሃሳብ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

2. ታታሪነት በምን የሚገልፅ ይመስላችኋል? ሰዎች ታታሪ ናቸው ሲባሉ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?

3. ‹‹ታታሪው ሰራተኛ›› በሚለው ርእስ ስለምን የምታደምጡ ይመስላችኋል?

## ተግባር አንድ፡- አዳምጦ መረዳት

**ሀ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሰረት በማድረግ በቃላችሁ መልስ ስጡ፡፡**

1. መንሱር የተወለደው የት አካባቢ ነው?
2. ባለታሪኩ ከወንድሞቹ የተለየ ያስባለው ምንድን ነው?
3. ለመንሱርና ወንድሞቹ ትምህርት ማቋረጥ ምክንያት የሆነው ምንድን ነው?
4. ታታሪው ሰራተኛ ከሚለው ምንባብ የተረዳችሁትን ሀሳብ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
5. መንሱር በልጅነቱ ምን መሆን ነበር የሚፈልገው? ፍላጎቱስ ተሳክቶለታል ብላችሁ ታስባላችሁ? መልሳችሁን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

ለ. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አረፍተ ነገሮች በሳጥኑ ውስጥ ከተቀመጡት ቃላት ክፍት ቦታዎችን አሟልታችሁ ፃፉ፡፡

ታላላቆቻቸውን፣ ባህል፣ ሀላፊነት፣ ውይይት፣ ነገ፣ ስፖርት፣ ቀልጣፋ

1. ታታሪነት የሁላችንም _____ሊሆን ይገባል፡፡
2. ልጆች_____ ማክበር አለባቸው፡፡
3. ብልህ ሰው ስለ _____ ያስባል፡፡
4. መፅሀፍትን በአግባቡ መያዝ የሁላችንም________ ነው፡፡
5. ሉዱያ ሁልጊዜም ጠዋት ጠዋት______ ትሰራለች፡፡
6. በጓደኞሞች መካከል የሚደረግ________ ለውጤት ያበቃል፡፡

## ክፍል ሁለት፡- ንባብ

### ሰነፍ ይከስራል ሰራተኛ ይከበራል

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች



1. ስእሉን ተመልክታችሁ የተረዳችሁትን ሃሳብ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

2. ‹‹ሰነፍ ይከስራል ሰራተኛ ይከበራል›› የሚል አባባል ብትሰሙ ምን ያስታውሳችኋል? መልሳችሁን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

3. በአካባቢያችሁ በስንፍና ምክንያት ለኪሳራ የተዳረገ ሰው ታውቃላችሁ? ለምን የከሰረ ይመስላችኋል? መልሳችሁን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

## ሰነፍ ይከስራል ሰራተኛ ይከበራል

በድሮ ጊዜ አንድ ሰውዬ ሰው በአለም ላይ ሲኖር ምን ዓይነት ስራ እየሰራ ቢኖር ይሻሳል እያለ ሃሳቡን በልቡ ሲያወጣና ሲያወርድ ነበር፡፡ ከዚያም እንዲህ አለ፡፡

‹‹መሬት አለኝ፤ ይህንን መሬቴን እህል ብዘራበትና አትክልት ብተክልበት ገንዘብ አገኝበታለሁ፤ መሬቱም ይለማል፡፡ ስለዚህ በሁለት በኩል ጥቅም አገኝበታለሁ›› አለ፡፡ ለዚህም የሚሆነውን ልዩ ልዩ የስራ መሳሪያዎች አሰናድቶ፣ አገልጋዮቹን ጠርቶ ‹‹በመሬቴ ላይ እህል ለመዝራትና የተለያዩ የአትክልት አይነቶችን ለመትከል አስቢያለሁና ስለዚህ ጠዋት ጠዋት ወደዚያ በመሄድ እንድትሰሩ›› ብሎ አዘዛቸው፡፡ ነገር ግን እሱ የትም እየዞረ ሲጠጣ፣ ሲጫወት፣ ሲፈነጥዝ ይውላል፡፡ ሰራተኞችም እሱ እንደሄደ ስለሚያወቁ ጊዜያቸውን በጨዋታ ያሳልፉ ነበር፡፡ ለሶስት አመት በዚህ መልኩ ከኖሩ በኋላ ከአትክልቱና ከእርሻው ያገኘውን ገንዘብ እንኳንስ ሃብት ሊኖረው የአገልጋዮቹን ልብስና ምግብ ሳይችልለት ቀረ፡፡

## የመሬቱ ባለቤት ሰውዬ በቀጣይ ምን የሚያደርግ ይመስላችኋል ?

የመሬቱ ባለቤት ይህ እንዳለወጠው ሲረዳ የመሬቱን እኩሌታ ሸጠው፤ ሌላኛውን እኩሌታ ደግሞ አከራየው፡፡ የተከራየውም ሰውዬ ሶስት ዓመት ሙሉ ለእርሻ፣ ለአትክልትና ለከብት እርባታ እየተጠቀመበት ኪራዩን ይከፍለው ነበር፡፡ ተከራዩም አንድ ቀን ያንን የቀረውን እኩሌታ እንዲሸጡለት ጠየቀው፡፡ ሰውዬውም በሃሳቡ ተስማማ፡፡ ‹‹እኔ በዘህ መሬት ሶስት አመት ሰርቼ አላተረፉኩበትም፡፡ አንተ ግን ከእኔ ተከራይተህ በየዓመቱ ኪራዩን እየከፈለክ ትርፋማም ሆነህበታል፡፡ ይህም ትርፋማ በመሆንህ ነው የቀረውን ልትገዛ የመጣኸው፡፡ ለመሆኑ ከዘሁ መሬት ነው ወይስ ከሌላ ተበድረህ ባገኘኸው ገንዘብ ነው?›› ብሎ ሲጠይቀው ‹‹ባንተ መሬት ላይ ሰርቼ ባተረፍኩት ነው›› ብሎ መለሱለት፡፡ ‹‹እኔ ስከስር አንተ ያተረፍከው እንዴት ነው ምክንያቱን ልትገልጽልኝ ትችላለህ?›› አለው፡፡ ተከራዩም ‹‹አንተ ጠዋት ስትነሳ አገልጋዮቹን ስሩ ትላለህ፤ እኔ ግን ሰራተኞቹን ኑ እንሂድ እንስራ እላችዋለሁ ምክንያቱ ይህ ብቻ ነው›› ብሎ መለሰለት፡፡

‹‹ሂዱ ስሩ በማለትና ኑ እንስራ በማለት መካከል ምን አይነት ልዩነት አለ?›› ብሎ አሁንም ደግሞ ጠየቀው፡፡ ‹‹ልዩነቱማ አንተ ጠዋት ተነስተህ አገልጋዮችህን ሂዱ ስሩ ብለህ ትልካቸውና አንተ ጨዋታና ፈንጠዝያ ወደሚገኝበት ቦታ እየሄድክ ገንዘብህና ጊዜህን በከንቱ ስታባክን ትውላለህ፡፡ አገልጋዮችህ ደግሞ ጊዜያቸውን በማላገጥ ያሳልፋሉ እንጅ ምንም ስራ አይሰሩም፡፡ አንተም አጠገባቸው ሆነህ ስለማትመለከታቸውና ስለማትቆጣጠራቸው

ልትቆጣቸው አትችልም፡፡ ስለዚህ ያንተ ጉዳት በሁለት በኩል ነው፡፡ በመጀመሪያ አንተ አትሰራም ደግሞም ገንዘብ ስታባክን ትውላለህ ሁለተኛ አገልጋዮችህም ምንም አይሰሩ፤ ሰነፎች ናቸው፡፡ ታዲያ አንተ ያልከሰርክ ማን ይክሰር፡፡ እኔ ብትለኝ ግን ጠዋት በማለዳ ተነስቼ ኑ እንሂድ እንስራ ብዬ ሰራተኞቼን ከፊቴ አስቀድሜ እሄዳለሁ፡፡ እዚያ ስንደርስ በአጭር ታጥቄ በመካከላቸው ሆኜ እስከማታ እሰራለሁ፡፡ ሰራተኞቼንም አብሬ በመሆን እቆጣጠራለሁ፡፡ እንደዚህ ሰርቼ እኔ ያላተረፍኩ ማን ያትርፍ ይኸውልህ ሂዱ ስሩ በማለትና ኑ እንሂድ እንስራ በማለት መካከል ያለው ትልቁ ልዩነት ይህ ነው፡፡›› አለው፡፡

ከበደ ሚካኤሌ (1999) ታሪክና ምሳሌ 1 ኛ መፅሃፍ፣ ገፅ 50 - 54 ተሻሽሎ የተወሰደ

## ተግባር አንድ፡- አንብቦ መረዳት

### ሀ. የሚከተለትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃል መልሱ፡፡

1. የሰው ልጅ በዓለም ሲኖር ስራ የመስራት ግዴታ አለበት ትላላችሁ?
2. ሰውዬው መሬት እያለው ለኪሳራ የተዳረገው በምን ምክንያት ነው?
3. አብዛኛውን ጊዜ በጨዋታና ፈንጠዝያ ማሳለፍያ ሊያስከትል የሚችለው ችግር ምንድን ነው?
4. ተከራዩ ሰውዬ የቀረውን መሬት እንዲሸጥለት የጠየቀው ለምን ፈልጎ ነው?
5. ባለመሬቱ ሰውዬ በሶስት አመት ውስጥ ያልተለወጠው በራሱ ነው ወይስ በሰራተኞቹ ችግር ይመስላችኋል? ምክንያቱን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ በፅሁፍ መልሱ፡፡

1. የመሬቱ ባለቤት እንዳላዋጣው ሲረዳ ምን አደረገ?

ሀ. ተጨማሪ መሬት ገዛ፡፡

ለ. የቀሪውን እኩሌታ ሸጠ፡፡

ሐ. አንደኛውን እኩሌታ አከራየ፡፡

መ. ለ እና ሐ መልሶች ናቸው ፡፡

2. መሬቱን የተከራየው ሰውዬ መሬቱን ለምን ለምን ይጠቀምበት ነበር?

ሀ. ለእርሻ ለ. ለአትክልት ስፍራ

ሐ. ለከብት እርባታ መ. ሁሉም

3. ‹‹ባንተ መሬት ላይ ሰርቼ›› ያለው ማን ነው?

ሀ. ተከራዩ ለ. ባለመሬቱ ሰውዬ

ሐ. ሰራተኞቹ መ. ሁሉም

4. ‹‹ኑ እንሂድ እንስራ›› የሚለው አረፍተ ነገር ምን የሚል ሃሳብ ያስተላልፋል?

ሀ. እናንተ ሂዱ እኔ እመጣለሁ፡፡

ለ. አብረን በአንድ ላይ እንስራ ፡፡

ሐ. ሰራተኞች ብቻ እንዲሰሩ መላክ፡፡

መ. ለብቻ መስራት

5.ያንተ ጉዳት በሁለት በኩል ነው ያለው ምንና ምኑን ነው?

ሀ.ሰውዬው ለራሱ አለመስራቱንና ገንዘብ ማባከኑ

ለ. አገልጋዮቹ ምንም አለመስራታቸው

ሐ. መሬቱን መሸጡንና ማከራየቱ

መ. ሀ እና ለ መልሶች ናቸው።

6. በምንባቡ መሰረት አለመስራት ከሚከተሉት በምን ይገለፃል?

ሀ. ስኬታማ በመሆን ለ. ለችግርና ለድህነት በመጋለጥ

ሐ. ሃብት በማፍራት መ. ረጂ በመሆን

**ተግባር ሁለት፡- ቃላት**

**ሀ. ተተኳሪ ቃላትን በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን አሟሉ።**

| |
|---|
| ማሰላሰል፣ አመለካከት፣ ፈንጠዝያ፣ መስራት፣ ትጋት፣ ትርፋማ፣ ብድር |

1. ሳምንቱን ምን መስራት እንዳለበት ተቀምጦ_______ ጀመረ።

2. ሰውዬው በስራው ውጤታማ በመሆኑ ምክንያት ከልጆቹ ጋር ቀኑን በ_______ አሳለፈ።

3. የሰው ልጅ ሰርቶ ለመለወጥ ለስራ ያለው_____ አዎንታዊ መሆን አለበት።

4. ወይዘሮ አስካለ በ__________ስለምትሰራ_________ ሆነች።

5. ከአቶ ካሳሁን ________ ወስጄ የንግድ ስራ ጀመርኩ።

**ለ. የሚከተሉትን ከምንባቡ የወጡ ሀረጋትና አረፍተ ነገሮች በሃሳብ አብረው የሚሄዱትን መርጣችሁ አዛምዱ፡፡**

**ምሳሌ፡-** በአግባቡ አለልሰራም -- ለድህነት ተዳረገ

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ገንዘብ ያባክናል | ሀ. ተጨማሪ መሬት ገዛ |
| 2. መሬት ተከራየ | ለ. አትክልት አለማ |
| 3. ጠንክሮ ሰራ | ሐ. ለኪሳራ ተዳረገ |
| 4. ብዙ ገንዘብ አገኘ | መ. ውሳኔ ላይ ደረሰ |
| 5. በጥልቀት አሰበ | ሠ. ውጤታማ ሆነ |

**ተግባር ሶስት፡- መፃፍ**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመመሪያው መሰረት በፅሁፍ መልሱ፡፡**

1. ‹‹ሰነፍ ይከስራል የሰራ ይከበራል›› በሚለው ሃሳብ ዙሪያ ተረቶችን ፈልጋችሁ በማንበብ የተረዳችሁትን ፍሬ ሃሳብ ፅፋችሁ ለጓደኞቻችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ፡፡
2. የቀረበላችሁን ምንባብ በድጋሚ በማንበብ ዋና ዋና ሃሳቦችን በአራት አረፍተ ነገሮች ፅፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

## ክፍል ሶስት፡- ቃላት

**ተግባር አንድ፡- በተመሳሳይ ሆሄ የሚጨርሱ ቃላት**

**ሀ. በሚከተለው ምሳሌ መሰረት የመጨረሻ ቅርፃቸው ወይም ሆሄያቸው የሚመሳሰሉ ቃላትን ፃፉ፡፡ ለእያንዳንዱ ቢያንስ ሶስት ሶስት ቃላት ፃፉ፡፡**

**ለምሳሌ፡-** ሀ. ገነባ፣ ተቀባ፣ አዘባ

ለ. ተመታ፣ ሁካታ፣ ችሎታ

1. ቀመሰ ______ ______ ______

2. ከበረ __________ _______ ____

3. ቃረመ __________ ______ __________

4. ከፈለ ________ _______ ________

5. ጋረደ ________ ______ ______

6. ተከፋ _________ _________ ________________

**ለ/ በ "ሀ" ስር ለቀረቡት ቃላት ተስማሚ የሆኑትን ከ "ለ" ረድፍ መርጣችሁ አዛምዱ፡፡**

**ምሳሌ፡-** የእግር -- ሹራብ

| <u>ሀ</u> | <u>ለ</u> |
|---|---|
| 1. የጣት | ሀ. ቤት |
| 2. የእጅ | ለ. ቀለበት |
| 3. ጥቁር | ሐ. መንገድ |
| 4. የሳር | መ. ሰዓት |
| 5. የአንገት | ሠ. ሹራብ |
| 6. የመኪና | ረ. ሀብል |

**ሐ. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍች ስጡ፡፡**

1. መለስተኛ

2. ደንታ ቢስ

3. ውዝግብ

4. ማሞገስ

5. ጭምት

6. ባለጸጋ

7. አደባ

## ክፍል አምስት፡- ፅህፈት

### ተግባር አንድ፡- መፃፍ

1. እያንዳንዳችሁ በሳምንት ውስጥ የምትሰሯቸውን ስራዎች በቅደምተከተል በአምስት አረፍተ ነገሮች በፅሁፍ አስፍሩ፡፡

2. ወደፊት ምን መስራት ትፈልጋላችሁ ወይም ምን መሆን ትፈልጋላችሁ? መስራት የምትፈልጉት ዓላማ ላይ ለመድረስ ምን ምን ተግባራትን ታከናውናላችሁ? የወደፊት እቅዳችሁን በስድስት አረፍተ ነገሮች በመፃፍ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋሰው

### ተግባር አንድ፡- አያያዦች

ሀ. የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች ተገቢውን አያያዥ ቃል ወይም ሀረግ በመምረጥ አሟሉ፡፡

**ነገር ግን፣ እንግዲህ፣ ምክንያቱም፣ ወይስ**

1. በጠዋት ተነስቶ ነበር____________ ከቤት አልወጣም፡፡

2. ጫማ_______ልብስ ይሻልሻል?

3. በተደጋጋሚ ስመክረው ነበር______ምንም ማድረግ አልችልም፡፡

4. የመጀመሪያው ክፍለ ጊዜ ትምህርት አመለጠው ________ በሰዓት አልደረሰም፡፡

ለ . የሚከተሉትን አያያዦች ተጠቅማችሁ አረፍተ ነገር መስርቱ።

1. ቢሆንም
2. አለበለዚያ
3. ይሁን እንጅ
4. ስለዚህ
5. ወይም
6. በስተቀር

## ተግባር ሁለት፡- ቅጥያዎች

ማስታወሻ ቅጥያዎች ቅጥያዎች በሶስት ይከፈላሉ።

ከቃል በፊት የሚገቡ፣ ከቃል በኋላ የሚገቡና በቃል መሃል የሚገቡ ናቸው።

1. ከቃል በፊት የሚገቡት

ለምሳሌ፡-

ሀ. አስ- = አስመረቀ

ለ. እየ- = እየሄደ

ሐ. ሲ- = ሲመጣ

2. ከቃል በኋላ የሚገቡ

ለምሳሌ፡-

ሀ. -ኦች = ልጆች

ለ. -ኣችሁ = በላችሁ

ሐ. -ዎች = በሬዎች

መ. -ኣን =መምህራን

## 3. በቃል መሀል የሚገቡ

**ለምሳሌ፡-**

ሀ.-ጫ- = አጫጭር

ለ.-ዣ- = ረዣዥም

ሐ.-ላ- = ወላለቀ   ወዘተ. የመሳሰሉት ቅጥያዎች ናቸው፡፡

ሀ. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቃላት ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ቅጥያዎችን እየጨመራችሁ አጣምሩ፡፡

| ተ.ቁ | ዋና ቃል | -ኦች | -ኡ | -ኣችሁ | -ዋ | -ህ | -ኣችን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ቅርስ | ቅርሶች | ቅርሱ | ቅርሳችሁ | ቅርስዋ | ቅርስህ | ቅርሳችን |
| 2 | ገንዘብ | | | | | | |
| 3 | ቤት | | | | | | |
| 4 | ዘመድ | | | | | | |
| 5 | ልብስ | | | | | | |
| 6 | ክፍል | | | | | | |
| 7 | አባት | | | | | | |
| 8 | ገንዘብ | | | | | | |

ለ. በሚከተሉት ቃላት ላይ የተጨመሩትን ቅጥያዎች ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ለይታችሁ ፃፉ፡፡

**ምሳሌ**፡- ንፁሃን  ዋና ቃል (ንፁህ)  ሲሆን ቅጥያው (-ኣን) ነው፡፡

1. ቃላት
2. ቤታችን
3. ሰባበረ
4. ላሞች
5. ፈልጋችሁ

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. አንድ በአካባቢያችሁ የምታውቁትን በስራው ታታሪ የሆነ ሰው በምሳሌነት ፅፋችሁ በመምጣት ለክፈል ጓደኞቻችሁ በንባብ አሰሙ፡፡

2. "ሰነፍ ይከስራል የሰራ ይከበራል" የሚለውን ምንባብ አንድ ጊዜ በየግላችሁ በለሆሳስ አንብቡ፡፡ ከዚያም የምንባቡን ፍሬ ሃሳብ በራሳችሁ አገላለፅ በሶስት አረፍተ ነገሮች ፅፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

3. ትምህርታችሁን ስትጨርሱ በምን ሙያ ላይ መሰማራት ትፈልጋላችሁ? የወደፊት እቅዳችሁን ግለፁ፡፡

4. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍች ስጡ፡፡

ሀ. ብሂል　　　　ሐ. ተፈረጀ

.ለ. ለሆሳስ　　　　መ. በትር

1. የሚከተሉትን አያያዦች በመጠቀም አረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

ሀ. ስለዚህ

ለ. እንጂ

ሐ. ስለሆነ

መ. ቢሆንም

# ምእራፍ ዘጠኝ

## ባህል

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ባዳመጣችሁት ምንባብ ውስጥ የተነሱ ጉዳዮች ላይ ልምምድ ታደርጋላችሁ፡፡
- ምንባቡን አንብባችሁ መልእክቱን ትረዳላችሁ፡፡
- በተሰጧችሁ ቃላት አረፍተ ነገር ትመሰርታላችሁ፡፡
- ለአዳዲስ ቃላት ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡
- በአረፍተ ነገር ውስጥ መስተዋድዶችን ትለያላችሁ፡፡

### ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

የእንቁጣጣሽ በዓል አከባበር



### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ስዕሉን ስትመለከቱ ምን ተገነዘባችሁ?
2. አበባዎች ስታዩ ምን ታስታውሳላችሁ?
3. በአካባቢያችሁ የሚከበሩ ታላላቅ ክብረ በአላትን ዘርዝሩ፡፡

## ተግባር አንድ፡- አዳምጦ መናገር

**ሀ. የሚከተለትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት መልሱን በቃል ተናገሩ፡፡**

1. የእንቁጣጣሽ በዓል በየአመቱ መቼ ይከበራል?
2. በእንቁጣጣሽ ወቅት የሚሰጡ አበባዎች የምን መገለጫዎች ናቸው?
3. የራሷ የዘመን አቆጣጠር ያላት ሀገር የትኛዋ ነች?
4. በጥንት ጊዜ ኢፌ መስቀል እየተባለች የምትጠራው ምንድን ነች?
5. በሀገራችን የእንቁጣጣሽ በዓል የምን መገለጫ ነው?

**ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ሃሳቡ ትክክል ከሆነ እውነት፣ ካልሆነ ደግሞ ሀሰት በማለት በቃል መልሱ፡፡**

1. የሰው ዘር መገኛ ናት የተባለችው ኢትዮጵያ ናት፡፡
2. በአዲስ ዓመት መጀመሪያ ልጆች ለወላጆችና ለጎረቤት የምኞት መግለጫ ፖስት ካርድ ይሰጣሉ፡፡
3. ደመናማ ሰማይ የሚገፈፍበት የተባለው የነሐሴ ወር ነው፡፡
4. እውነተኛ እንቁጣጣሽ የሚለው ቃል ግጫ ነው፡፡
5. እንቁጣጣሽ በየሁለት ዓመቱ የሚከበር በዓል ነው፡፡

## ተግባር ሁለት፡- መናገር

በእንቁጣጣሽ ወቅት የሚዜሙ ወይም የሚባሉ ጨዋታዎችን አጥንታችሁ በመምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

## ተግባር ሶስት፡- ቃላት

**ሀ. በ "ሀ" ስር ለተዘረዘሩት ቃላት ከ "ለ" ስር ተመሳሳያቸውን በመፈለግ አዛምዱ፡፡**

| <u>ሀ</u> | <u>ለ</u> |
|---|---|
| 1. ጨለማ | ሀ. የሳር ዓይነት |
| 2. አውደ ዓመት | ለ. መታታት |
| 3. የምስራች | ሐ. ፅልመት |
| 4. ተንቆጠቆጠ | መ. የደስታ መግለጫ |
| 5. ኩልል | ሠ. አሸበረቀ |
| 6. እንግጫ | ረ. ክብረ በዓል |
| 7. ኮረብታዎች | ሰ. ጥርት |
| 8. መጎንጎን | ሸ. ጉብታዎች |

**ለ. የሚከተሉትን በ"ሀ" ረድፍ የቀረቡን ቃላት በ"ለ" ረድፍ ካሉት ጋር ተቃራኒያቸውን በመፈለግ አዛምዱ፡፡**

| <u>ሀ</u> | <u>ለ</u> |
|---|---|
| 1. የመጀመሪያ | ሀ. ተራራ |
| 2. ማሸብረቅ | ለ. ማደብዘዝ |
| 3. በዓል | ሐ. የመጨረሻ |
| 4. ሜዳ | መ. መጥፎ |
| 5. መልካም | ሠ. ንጥል |
| 6. ጥቅል | ረ. አዘቦት |

## ተግባር አራት፡- መፃፍ

1. በአካባቢያችሁ በዓል ሲመጣ የሚዘጋጁ ባህላዊ ምግቦችን ፅፋችሁ በመምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

2. በአመት በአል እለት የሚለበሱ ባህላዊ አልባሳትን ዝርዝር ፅፋችሁ በመምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስደምጡ፡፡

3. አንድ የክብረ በዓል አከባበር ስርዓትን በመምረጥ ፅፋችሁ በመምጣት በክፍለ ውስጥ ለመምህራችሁና ለጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

## ክፍል ሁለት፡- ንባብ

### ባህል

### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ከስዕል የተረዳችሁትን ሃሳብ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
2. ባህል ምንድን ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?
3. በአካባቢያችሁ ሰርግ ሲኖር ምን ዓይነት ስነ ስርዓት ይከናወናል?





### ባህል

“ባህል ምንድን ነው?” ተብለን ብንጠየቅ ሁላችንም የተለያየ አይነት መልስ ልንሰጥ እንችላን፡፡ እያንዳንችን የአንድ ማህበረሰብ አባል በመሆናችን ባህል አለን፡፡ ባህል የአንድን ማህበረሰብ ማንነት የሚያንፀባርቅ ነው፡፡ በሀገራችን በርካታ ብሄር ብሄረሰቦች ይገኛሉ፡፡

ሁሉም ብሄሮች የማንነታቸው መገለጫ ባህል አላቸው፡፡ ከነዚህም ውስጥ የጋብቻ ስነ ስርዓት፣ የለቅሶ ስነ ስርኣት፣ የልደት አከባበር ስርዓት፣ የአለባበስ ስርዓት፣ የተለያዩ የበዓል አከባበሮች፣ ከዓመት በአል ጋር ተያይዘው የሚዘጋጁ የተለያዩ ባህላዊ ምግቦች፣ በበአል ወቅት የሚለበሱ የተለያዩ አልባሳት፣ ባህላዊ የፀጉር አሰራር ፣ ለማጌጥ ወይም ለመዋብያነት የምንጠቀምባቸው ባህላዊ ጌጣ ጌጦች ሁሉ የባህል መገለጫዎች ናቸው፡፡

ባህል ለሰው ልጅ ምን አገልግሎት ይኖረዋል ብላችሁ ትገምታላችሁ ?

ባህል ለማህበረሰባችን እንደ ህግ ሆኖ ያገለግላል፡፡ የእርቅና የለቅሶ ስርዓት እንደ ምሳሌ ማንሳት እንችላለን፡፡ የእርቅ ስርዓት ሰዎች እርስ በርሳቸው ሲጣሉ የሚያስታርቁበት አንድ መንገድ ነው፡፡ ከሁለቱም ባለጋራ ወገን ሽማግሌዎች ተቀምጠው ጉዳዩን ወደ ህግ አካላት ሳይወስድ በአካባቢያቸው በልማድ የሚጠቀሙበትን የግጭት አፈታት ህግ ተከትለው እርቀ ሰላም እንዲወርዱ ያደርጋሉ፡፡ ይህ በሽምግልና ግጭት የሚፈታበት ስርዓት እንደየማህበረሰቡ ባህል የተለያየ ሊሆን ይችላል፡፡

ለአንድ ማህበረሰብ ሌላው የባህል መገለጫው የለቅሶ ስነ ስርዓት ነው፡፡ የሰው ልጅ በምድር ላይ ተወልዶ ሲኖር በርካታ የህይወት ምእራፎችን ያሳልፋሉ፡፡ ከእነዚህ የህይወት ምእራፎች አንዱና የመጨረሻው ሞት ነው፡፡ ሰው ሲሞት የቀብር ስርዓት ሲካሄድ ለቀስተኞች የአስከሬን ሽኝት የሚያደርጉበት መንገድ አንዱ ማሳያ ነው፡፡ ለቅሶ ሲኖር የአካባቢው ሰውና ወዳጅ ዘመድ ተሰብስቦ ሃዘንተኛ ቤተሰብን ያጽናናሉ፤

ያስተዛዝናሉ፡፡ አብረው በመገኘት የአስከሬን ሽኝት ያደርጋሉ፡፡ የሽኝቱ ስነ ስርዓትም እንደየማህበረሰቡ ባህል የተለያየ ነው፡፡

በአጠቃላይ ባህል ለአንድ ማህበረሰብ የማንነቱ ማንፀባረቂያ ብቻ ሳይሆን አንዱ ከአንዱ ጋር ህብር ፈጥሮ እንዲኖር የሚያስችል ነው፡፡ ባህል ከሰው ልጅ ጋር እጅግ የተቆራኘ ሀብት ነው ፡፡ የባህል ባለቤት መሆን የሚቻለው ደግሞ የማህበረሰብ አባል መሆን ሲቻል ነው፡፡ እያንዳንዱ ማህበረሰብም የራሱ ባህል አለው፡፡ ይህም የተለያየ የማህበረሰብ ባህል ደግሞ ብዙ ባህሎች እንዲኖሩ ያደርጋል፡፡ በዚህ ምክንያት ኢትዮጵያችን ባለብዙ ባህል ባለቤት በመሆን የታደለች ሀገር ናት፡፡

ተግባር አንድ፡- አንብቦ መረዳት

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃል መልሱ፡፡**

1. የምንኖርበት ማህበረሰብ የራሱ ባህል አለው ትላላችሁ? መልሱን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
2. ባህል እንዴት የማንነት መገለጫ ሊሆን ይችላል?
3. የባህል መገለጫ መንገዶች ምን ምን ናቸው? ዘርዝራችሁ ተናገሩ፡፡
4. ሀገራችን ብዙ ባህል እንዲኖራት ያስቻላት ምንድን ነው?
5. እንደ ልደትና የሰርግ ስርአት ያሉት የባህል መገለጫዎች ናቸው ማለት ይቻላል?

**ለ. ምንባቡን መሰረት በማድረግ ትክክል የሆነውን ሃሳብ እውነት፣ ስህተት የሆነውን ደግሞ ሀሰት በማለት በፅሁፍ መልሱ፡፡**

1. ማንኛውም ማህበረሰብ የራሱ ባህል አለው፡፡

2. ባህላዊ የፀጉር አሰራር የባህል ማሳያ ሊሆን ይችላል፡፡

3. በባህላዊ መንገድ እርቀ ሰላም መፍጠር አይቻልም፡፡

4.ማንኛውም ማህበረሰብ የተለያየ ባህል ቢኖረውም የሚያስተሳስረው አንዳች ነገር ግን አለው፡፡

5. ባህል ከሰው ልጅ ጋር ብዙም ቁርኝት የለውም፡፡

## ተግባር ሁለት፡- ቃላት

**ሀ. ከዚህ በታች ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ተመሳሳይ ፍች ስጡ፡፡**

1. ባላጋራ
2. ባህል
3. ማሳያ
4. ህብር
5. መዋብያ
6. ማስታረቅ

**ለ. ለሚከተሉት ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ተቃራኒ ፍች ስጡ፡፡**

1. ውልደት
2. መቆራኘት
3. አንድነት
4. ህጻን
5. ማውረድ

**ሐ. በሚከተሉት ቃላት አረፍተ ነገሮችን መስርቱባቸው፡፡**

1. ባህል
2. ሰላም
3. ማህበረሰብ
4. ይቻላል
5. አለው

## ተግባር ሶስት፡- መፃፍ

1. በአካባቢያችሁ የለቅሶ ስርዓት እንዴት እንደሚከናወን ወላጆቻችሁን ጠይቃችሁ ፅፋችሁ በመምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ፡፡

2 በአካባቢያችሁ የባህላዊ ምርቃት ስነ ስርዓትን ጠይቃችሁ ፅፋችሁ በመምጣት ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡ ለምሳሌ፡- አባቶች ልጆችን ሲመርቁ የሚገለፅ


3.ልደታችሁን ስታከብሩ የምታደርጓቸውን ስርዓቶችን ፅፋችሁ በመምጣት ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡


## ክፍል ሶስት፡- ቃላት


### ተግባር አንድ፡- የቃላት ተመሳሳይ ፍች

**ሀ. በምሳሌው መሰረት ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍች ስጡ፡፡**

**ምሳሌ፡-**








**ለ. በ "ሀ" ስር ለቀረቡት ቃላት ከ "ለ" ስር ተቃራኒ ፍቻቸውን በመምረጥ አዛምዱ፡፡**

| <u>**ሀ**</u> | <u>**ለ**</u> |
| --- | --- |
| 1. ሸካራ | ሀ. ድርቅ |
| 2. መዘግየት | ለ. አነሰ |
| 3. ንፉግ | ሐ. መፍጠን |
| 4. ልምላሜ | መ. ለጋስ |
| 5. ገዘፈ | ሠ. ፈዘዘ |
| 6. ቀልጣፋ | ረ. ለስላሳ |

## ክፍል አራት፡- ፅህፈት

### ተግባር አንድ፡- መፃፍ

ከዚህ በታች የቀረቡትን ቃላት ቅደም ተከተል በማስተካከል ተገቢውን ስርዓተ ነጥቦች ተጠቅማችሁ አረፍተ ነገሮቹን እንደገና አስተካክላችሁ ፃፉ፡፡

1. ፅጌረዳ፣ ወንበር፣ ተቀመጠች፣ ላይ፣ ፀሀይ፣ አውጥታ
2. ወደቀ፣ ህፃኑ ልጅ፣ ተደናቅፎ፣ ሲሮጥ

3. ራቢያ፣ ተመረቀች፣ በጥሩ፣ ውጤት

4. ሂሩት፣ የሂሳብ፣ ስራች፣ የቤት ስራ

5. ችግኝ፣ ሳዱቅ፣ ተከለ

6. ሙዚቃ፣ ያሬድ፣ ይወዳል፣ ማዳመጥ

7. እወዳለሁ፣ እኔ፣ መዝናኛ፣ መሄድ፣ ስፍራ

## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

### ተግባር አንድ፡- መስተዋድድ

ማስታወሻ

መስተዋድዶች ከስም በፊት ወይም በኋላ በመምጣት ስሙን ከሌላ ቃል ወይም ሀረግ ጋር የማዋደድ ወይም የማያያዝ ተግባር አላቸው ፡፡ መስተዋድዶች የሚባሉት፡- ስለ፣ እንደ፣ ከ፣ ለ፣ ወደ፣ አጠገብ፣ ባሻገር፣ ወዲህ፣ ላይ፣ ታች፣ ውስጥ ወዘተ. የመሳሰሉት ናቸው፡፡

**ሀ. የሚከተሉትን መስተዋድዶች ምሳሌውን መሰረት በማዴረግ ከስም ለይታችሁ አስምሩባቸው፡፡**

**ምሳሌ፡-** ቤት = አጠገብ ("ቤት" ስም ሲሆን "አጠገብ" ደግሞ መስተዋድድ ነው፡፡)

ከ = ሶዶ ( "ከ" መስተዋድድ ሲሆን "ሶዶ" ደግሞ ስም ነው፡፡)

1. ዛፍ ላይ

2. ስለ ትምህርት

3. ለወንድሙ

4. ሆሳዕና ድረስ

5. ከወንዝ ማዶ

6. ወደ ትምህርት ቤት

**ለ. ከዚህ በታች በቀረበው ሰንጠረዥ ውስጥ መስተዋድድ የሆኑትን ቃላት ብቻ ለይታችሁ ፃፉ፡፡**

ከ፣ ልጅ፣ ጥቁር፣ ወደ፣ ውስጥ፣ ምርኩዝ፣ ምንኛ፣ እንደ፣ ክብ፣ እስከ፣ ላይ፣ ትንሽ፣ ገዙ፣ አጠገብ፣ ቶሎ፣ ብልህ፣ ታች…

**ሐ. ከዚህ በታች የቀረቡትን መስተዋድዶች በመጠቀም አረፍተ ነገር መስርቱ፡፡**

1. እስከ
2. አጠገብ
3. ድረስ
4. እንደ
5. ወዲህ

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. በበዓላት ወቅት በሬዲዮ ወይም በቴሌቭዥን የሚተላለፉ ባህላዊ ዘፈኖችን አዳምጣችሁ፤ ያዳመጣችሁትን ባህላዊ ዘፈን በቃል በማጥናት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

2. ከተለያዩ የበዓላት አከባበር ስርዓቶች ውስጥ አንዱን በመምረጥ ስለዚያ ባህል ጠይቃችሁ ወይም አንብባችሁ በመምጣት የተረዳችሁትን በፅሁፍ ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡

3. ሁለት ሁለት ስምና ግስ የሆኑ ቃላትን በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡

4. ለሚከተሉት ቃላት ሁለትና ከዚያ በላይ ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ፡፡

ሀ. ስራ ለ. መንስኤ ሐ. አፀና

5.የሚከተሉትን መስተዋድዶች በመጠቀም አረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

ሀ. እንደ ለ. ጋር ሐ. ስለ መ. ወደ

# ምዕራፍ አስር

## ገበያ

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- የቀረበላችሁን ምንባብ አዳምጣችሁ መልዕክቱን ትናገራላችሁ፡፡
- በክፍል ደረጃችሁ ያነበባችሁትን ፅሁፍ ዋና ሀሳብ ታብራራላችሁ፡፡
- ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ፍች ትሰጣላችሁ፡፡
- አያያዥ ቃላትን በመጠቀም ድርብ አረፌተ ነገር ትፅፋላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

ቅድስትና የገበያ ውሎዋ



## ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. በስዕሉ ላይ ምን ምን ነገሮችን ተመልከታችሁ?
2. ከወላጆቻችሁ ጋር ገበያ ሄዳችሁ ታውቃላችሁ?
3. ገበያ ውስጥ ምን ምን ነገሮች ይገኛል፣ ብላችሁ ትገምታላችሁ?

## ተግባር አንድ፡- አዳምጦ መረዳት

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።**

1. ባለታሪኳ ወደ ገበያ የሄደችው ምን ለማድረግ ነበር?
2. የቅድስት አማርኛ መምህር ምን ፅፉ እንድትመጣ አዘዟት?
3. ከከተማው ትንሽ ወጣ ብላ ሰፊ ሜዳ ላይ ነው የተባለው ምኑ ነው?
4. ቅድስት ገበያ ለመሄድ ወላጆቿ አብረዋት ባይሆኑ ብቻዋን ትሄድ ነበር?
5. ባህላዊ የግብይት ስርዓት የሚባለው ምንድን ነው?

**ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ሃሳቡ ትክክል ከሆነ እውነት፣ ካልሆነ ደግሞ ሀሰት በማለት መልሳችሁን በቃል ተናገሩ። በምክንያት አስደግፋችሁ ግለፁ።**

1. ወላጆቿ የቅድስትን ጥያቄ ለመመለስ ፈቃደኛ አልነበሩም።
2. ቅድስት ገበያ ሄዳ የሚያስፈልጓትን ቁሳቁሶች ሁሉ ገዛች።
3. እነቅድስት የሄዱበት ገበያ ገዥና ሻጩ ያለ ክርክር ይገበያዩበት ነበር።
4. በላስቲክ የተወጠሩት ሸራዎች ውስጥ ሸቀጦች በብዛት ይታዩ ነበር።
5. ቅድስት ገበያ ውስጥ ማስታወሻዋን ትፅፍ የነበረው በግሏ ማጥናት ስለፈለገች ነው።

## ተግባር ሁለት፡- መናገር

ጥንድ ጥንድ በመሆን የሚከተለውን ጭውውት አጥንታችሁ በክፍል ውስጥ አቅርቡ።

ከዚህ በታች ነቢያት ሻጭ ነጋዴ ሆና የቀረበችበት፣ ይልቃል ደግሞ ገዥ ሆኖ ቀርቧል። በሁለቱ መካከል የተደረገውን ምልልስ መነሻ በማድረግ እናንተም መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት ጭውውት አድርጉ።

**ነብያት** የልብስ፣ የጫማና ሌሎችም የተለያዩ ነገሮች መሸጫ አላት።

**ይልቃል**፡- ጫማ ይኖርሻል?

**ነብያት**፡- አዎ! መምረጥ ትችላለህ፤ ቁጥር ንገረኝ።

**ይልቃል**፡- ሰላሳ ስድስት ነው።

**ነቢያት**፡- ይኸውልህ የተለያዩ ቀለም አማራጮች አለኝ።

**ይልቃል**፡- ጥቁር ጫማ ነው የምፈልገው።

**ነቢያት**፡- አለ። ዋጋው ሰባት መቶ ሃምሳ ብር ነው።

## ተግባር ሶስት፡- ቃላት

**ሀ. ለሚከተሉት ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ተመሳሳይ ፍቾ ስጡ፡፡**

1. አድናቆት
2. ቅኝት
3. በተመስጦ
4. ዘገባ
5. ግብይት

**ለ. ለሚከተሉት በ"ሀ" ረድፍ ለቀረቡት ሀረጋት ተስማሚያቸውን ከ "ለ" ረድፍ እየመረጣችሁ አዛምዱ፡፡**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ሸቀጥ አከፋፋይ | ሀ. የመሸጫ ቦታ |
| 2. ሰፊ ሜዳ | ለ. ጅምላ ሻጭ |
| 3. የገበያ ተራ | ሐ. በተለምዶ የሚከናወን የንግድ ስርዓት |
| 4. ባህላዊ ግብይት | መ. የተንጣለለ መስክ |
| 5. የድንጋይ ካብ | ሠ. የመሸጫ መደብ |

## ተግባር አራት፡- መፃፍ

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመመሪያው መሰረት በፅሁፍ መልሱ፡፡**

1. በአካባቢያችሁ ወደሚገኝ ገበያ ከወላጆቻችሁ ጋር በመሄድ ባህላዊ የግብይት ስርዓቱ እንዴት እንደሚከናወን ፅፋችሁ በመምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ፡፡

2. በባህላዊ የግብይት ስርዓት ከዘመናዊ የግብይት ስርዓቱ በምን እንደሚለይ በሰፈራችሁ አንድ የምታውቁትን ነጋዴ ጠይቃችሁ ፅፋችሁ በመምጣት ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡ በፅሁፋችሁ ውስጥ ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ መጠቀማችሁን አትርሱ፡፡

## ክፍል ሁለት፡- ንባብ

### አዲስ አበባና የገበያ ቦታዎቿ



### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ስዕሉን በመመልከት የተረዳችሁትን ሀሳብ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

2. በአካባቢችሁ የምታውቋቸውን የገበያ ስፍራዎች ጥቀሱ፡፡

3. ‹‹አዲስ አበባና የገበያ ቦታዎቿ›› የሚለው ምንባብ ስለምን የሚያስረዳ ይመስላችኋል?

## አዲስ አበባና የገበያ ቦታዎቿ

አዲስ አበባ የሀገሪቷ ዋና ከተማ እንደመሆኗ ከፍተኛ የሆነ የንግድ እንቅስቃሴ የሚታይባት ከተማ ናት፡፡ በከተማዋ ትልልቅ ዘመናዊና ባህላዊ የግብይት ስርዓቶች በስፋት ይከናወኑባታል፡፡ የተለያዩ የግብይት ቦታዎችም በብዛት አሏት፡፡ ዋና ዋናና ታዋቂ የግብይት ስፍራዎች ከሚባለት ውስጥ እንዱ መርካቶ፣ ሽሮ ሜዳ፣ ሾላ ገበያ፣ ካራና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡ የመርካቶ ገበያ ግዙፍ የገበያ ቦታ ሲሆን ከጅምላ ማከፋፈያ አንስቶ እስከ ችርቻሮ መሸጫ

ድረስ ሁሉም በአቅሙ የሚገበያይበት ቦታ ነው፡፡ መርካቶ ባህላዊና ዘመናዊ ግብይት ስርዓት በጥምረት የሚቀርቡበት ቦታ ነው፡፡ በመሆኑም ከሀገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች የሚመጡ በርካታ ነጋዴዎች የሚገናኙበት የገበያ ስፍራ ነው፡፡ ይህ ስፍራ ከፍተኛው የግብይት ስርዓት የሚካሄድበት በመሆኑ በአብዛኛው በገዥና ሻጭ ወይም በሰው ብዛት የተጨናነቀ ነው፡፡ ሌላኛው በከተማዋ የሚገኘው የገበያ ቦታ ሽሮ ሜዳ ነው፡፡ ሽሮ ሜዳ ሀገር በቀል የሆኑ ባህላዊ አልባሳት የሚገኙበት ቦታ ነው፡፡ ገበያው ውስጥ ገብቶ ግራና ቀኙን ለተመለከተ በተለያየ ህብረ ቀለማት ያሸበረቁት ባህላዊ አልባሳት “ሳትገዙኝ አትለፉኝ” የሚሉ ይመስላሉ፡፡ ከዚህም የተነሳ አብዛኛውን ጊዜ ወደ ገበያ ስፍራ የገባ ሰው ሳይገዛ ባድ እጁን አይወጣም፡፡ በእለቱ ገንዘብ ባይኖረው እንኳ ተመልሶ ለመሄድ ቀጠሮ የሚያዝለት የገበያ ስፍራ ነው፡፡ በከተማዋ በተለይ በዓመት በዓል ወቅት በእንስሳት ግብይት የሚታወቁ ቦታዎችም አሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ የሾላ ገበያና ካራ ይጠቀሳሉ፡፡ የሾላ ገበያ ከእንስሳት በተጨማሪ የተለያዩ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ነገሮች በስፋት የሚገኙበት ነው፡ ፡ የሾላ ገበያ የተለያዩ የንግድና የፍጆታ እቃዎች በተመጣጣኝ ዋጋ ይቀርቡበታል ከሚባሉት ስፍራዎች አንዱ ነው፡፡ በቁም እንስሳት ግብይትም ዶሮ፣ በግና ፍየል ከጠቦት እስከ ሙክት አቅሙ በቀፈደ መጠን የእርድ በሬም የሚቀርብበት ገበያ ነው፡፡ የካራ ገበያም በስፋት በቁም እንስሳት ግብይት የሚታወቅ ነው፡፡ በመሆኑም በዓመት በዓሉ ዋዜማ የተለያዩ ለእርድ የሚውሉ የቁም

እንስሳት ለማግኘት ወይም ለመግዛት ከተለያዩ የከተማዋ ክፍሎች ሰዎች በብዛት ወደዚያ ስፍራ በመሄድ ይገበያያሉ፡፡

## ተግባር አንድ፡- አንብቦ መረዳት

**ሀ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ በቃል መልስ ስጡ፡፡**

1. በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚታወቁ ዋና ዋና የገበያ ቦታዎችን ዘርዝሩ፡፡
2. አዲስ አበባ ውስጥ በትልቅነቱ የሚታወቀው የገበያ ቦታ የትኛው ነው?
3. የሾሮ ሜዳ ገበያ የሚታወቀው በምን የግብይት አይነት ነው?
4. ከምንባቡ የተረዳችሁትን ዋና ሀሳብ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

**ለ. በምንባቡ መሰረት ትክክል ከሆነ እውነት፣ ስህተት ከሆነ ሀሰት በማለት መልሳችሁን በቃል ተናገሩ፡፡**

1. ከጅምላ ማከፋፈያ እስከ ችርቻሮ ንግድ ሁሉም እንደየአቅሙ የሚገበያይበት ቦታ መርካቶ ነው፡፡
2. አዲስ አበባ ከተማ ዘመናዊ የግብይት ስርዓት ብቻ የሚከናወንባት ከተማ ናት፡፡
3. ባዳመጣችሁት ምንባብ ውስጥ በተጠቀሱት የገበያ ስፍራዎች በሁሉም ቦታ የቁም እንስሳት ብቻ ይሸጣሉ፡፡
4. ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በመምጣት የሚገበያዩበት ትልቁ ቦታ ሾላ ገበያ ነው፡፡

## ተግባር ሁለት፡- መናገር

1. ወላጆቻችሁ ብዙ ጊዜ የሚገበያዩበትን ቦታ ምን ምን ነገሮች እንደሚሸጡ ጠይቃችሁ ለመምህራችሁና ለክፍሉ ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

2. ገበያ የሚለውን ቃል ስትሰሙ በሃሳባችሁ የሚመጣውን ነገር በፅሁፍ ካዘጋጃችሁ በኋላ ለምመህራችሁ በቃል አቅርቡ፡፡

## ተግባር ሶስት፡- ቃላት

**ከዚህ በታች በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍች ስጡ፡፡**

1. የተለያዩ <u>የመገበያያ ስፍራዎች</u> በከተማችን ውስጥ ይገኛሉ፡፡

2. መርካቶ ውስጥ <u>የጅምላ ንግድ</u> የተለመደ ነው፡፡

3. ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚመጡ <u>በርካታ</u> ነጋዴዎች አሉ፡፡

4. አብዛኛው <u>የግብይት ስፍራ</u> በሻጭና ገዥ የተጨናነቀ ነው፡፡

5. የካራ ገበያ በስፋት <u>በቁም እንስሳት</u> ግብይት የሚታወቅ ነው፡፡

## ተግባር አራት፡- መፃፍ

1. መርካቶ ውስጥ ያሉትን የተራ ስሞች ወላጆቻችሁን ጠይቃችሁ ፅፋችሁ በመምጣት ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

2. ወላጆቻችሁ ልብስ ወይም ሌላ ነገር ሲገዙ ከሻጩ ጋር ያለውን የዋጋ ክርክር ጠይቃችሁ ፅፋችሁ በመምጣት ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

## ክፍል ሶስት፡- ቃላት

### ተግባር አንድ፡- ተቃራኒና ጥምር ቃላት

**ሀ. ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን በፅሁፍ ስጡ፡፡**

1. ቸከለ 2. ዝምተኛ 3. ታላቅ

4. ተናወጠ 5. አዋደደ

**ማስታወሻ**

**ልብ አድርቅ፣ ሆደ ሰፊ፣ ሰማይ ጠቀስ፣ ልቦለድ፣ ቃለ አጋኖ የመሳሰሉት ጥምር ቃላት ይባላሉ፡፡**

**.ለ. በ "ሀ" ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳያቸውን ከ "ለ" ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ፡፡**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. እጀ ሰባራ | ሀ. ዋጋ አወረደ |
| 2. ዋጋ ሰባሪ | ለ. ባለጌ |
| 3. ስር ሰደደ | ሐ. ያልረባ ስራ |
| 4. ስመ ጥር | መ. ገናና፣ ዝነኛ |
| 5. አይን አውጣ | ሠ. ተጠናከረ |

**ሐ. በሚከተሉት ቃላት አረፍተ ነገር መስርቱ፡፡**

1. ወበቅ 2. ቀለብ 3. በረከት

4. ማዳከም 5. መዳረሻ

## ክፍል አራት፡- ፅህፈት

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በፅሁፍ መልሱ፡፡**

1. ‹‹አዲስ አበባ እና የገበያ ቦታዎቿ›› የሚለውን ምንባብ አንድ ጊዜ በጥሞና ደግማችሁ አንብቡ፡፡ ከዚያም የእያንዳንዱን አንቀፅ ዋና ሃሳብ ለይታችሁ አውጡ፡፡ ዋና ሃሳቡን በራሳችሁ ሃሳብ አብራርታችሁ ፃፉ፡፡ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ መጠቀማችሁን አትርሱ፡፡

2. በቡድን በመሆን በአካባቢያችሁ ወደሚገኝ አንድ የልብስ መሸጫ በመሄድ የዋጋ ዝርዝር ጠይቃችሁ በመምጣት ዘገባ ፅፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

## ተግባር አንድ፡- አያያዦችን መለየት

**ሀ. በሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን አያያዦች ለይታችሁ አስምሩባቸው፡፡**

1. አክስቴ እሁድ ወይም ሰኞ ትመጣለች፡፡
2. ዛሬ ከባድ ዝናብ እየጣለ ቢሆንም ትምህርት ቤት መሄድ አለብኝ፡፡
3. ገበያ የሄድኩት የዓመት በዓል ዶሮ ልገዛ እንጂ ልብስ ለመግዛት አይደለም፡፡
4. ዛሬ ኳስ ጨዋታ ለማየት እሄደለሁ፤ ስለዚህ ስራዬን በጊዜ መጨረስ አለብኝ፡፡
5. ፈተና እየደረሰ ስለሆነ ሁላችንም ማጥናት አለብን፡፡

**ለ. ከዚህ በፊት በቀደሙት ምዕራፎች ያነሳናቸውን የቃል ክፍሎች ለማስታወስ ሞክሩ፡፡ ከዚህ በታች ስም፣ የስም ገላጮች፣ ግስ፣ የግስ ገላጮችና መስተዋድዶች ተደባልቀው ቀርበዋል፡፡ እያንዳንዳቸውን በየምድባቸው ለይታችሁ ፃፉ፡፡**

ወደ፣ ክፉ፣ ቀጭን፣ ገነባ፣ ምንኛ፣ ናቸው፣ ልዑል፣ ግብርና፣ ቶሎ፣ አጠገብ፣ አስተዋለ፣ ሀብት፣ ያፌት፣ ገና፣ ስለ፣ ገመተ፣ አስከ፣ ንፉግ፣ ክፉኛ፣ የዋህ፣ አሁን፣ ላይ፣ ጎበዝ…

1. ስም …………. …………. …………. …………. ……

2. የስም ገላጭ…………. …………. …………. …………. …

3. ግስ …………. …………. …………. …………. ……

4. የግስ ገላጭ…………. …………. …………. …………. …

5. መስተዋድድ…………. ………… ………… ………… ………

**ሐ. የሚከተሉትን ያልተሟሉ አረፍተ ነገሮች በተገቢው ቃል አሟሉ፡፡**

**አነበበ፣ ስለ፣ እስከ፣ ገበያ፣ አንብቡ፣ ጎበዝ፣ ጥቁር፣ በፍጥነት**

1. …………. የተለያዩ ነገሮች የሚሸጡበት ቦታ ነው፡፡
2. አየለች ከቤት …………. ወጣች
3. በመማሪያ መፅሃፍ ላይ ያለውን ምንባብ በየግላችሁ ………….
4. …………. ነጋዴ በመሆኑ ትልቅ ደረጃ ላይ ደረሰ፡፡
5. ከቤታችን …………. ትምህርት ቤት ድረስ በእግሬ መጣሁ፡፡

**መ. የሚከተሉትን አያያዥ ቃላት ወይም ሀረጋት በመጠቀም አረፍተ ነገር መስርቱ፡፡**

1. ሆኖም 2. ነገር ግን 3. ይሁን እንጅ 4. ወይም 5. እና

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. ባህላዊና ዘመናዊ የግብይት ስርዓትን በተመለከተ በቴሌቭዥን የሚተላለፉ ዘገባዎችን አዳምጣችሁ በማስታወሻችሁ በመያዝ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል ተርኩላቸው፡፡

2. ስለሻጭና ገዥ የሚያነሱ ፅሁፎችን ፈልጋችሁ አንብቡ፡፡ ያነበባችሁትን ፅሁፍ ዋና ሀሳብ በማስታወሻ ደብተራችሁ በመፃፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

3. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍች ስጡ፡፡

ሀ. ውጥረት ለ. መጠጊያ ሐ. እንደልብ መ. ባለጠጋ

4. የሚከተሉትን ቃላት በመጠቀም ድርብ አረፍተ ነገሮችን ፃፉ፡፡

ሀ. ቢሆንም ለ. ስለሆነም

5.የሚከተሉትን አያያዦች በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡

ሀ. ግን ለ. ወይስ ሐ . ከዚያም

# የቃላት ፍች

| ቃል | ፍች |
|---|---|
| ሀያል | ጠንካራ፣ የማይሸነፍ፣ ብርቱ፣ ሀይለኛ |
| ሁነኛ ሰው | ታማኝ፣ ሀቀኛ፣ ተስማሚ |
| በሽታ፣ | ህመም፣ደዌ፣ ጤና ማጣት |
| ህብረት ፡ | የመረዳዳት፣ የመተባበር፣ የመተጋገዝ ሁኔታ |
| ለማ፡ | ቀና አደረገ፣ በለፀገ፣ ለመለመ |
| ለገሰ፡ | መለገስ፣ መቸር፣ መስጠት |
| መሄድ፡ | መራመድ፣ መገስገስ |
| መላ | ዘዴ፣ብልሃት፣ |
| ማሰብ፣ | ማስተዋል መመኘት |
| ማፍቀር፣ | መከጀል፣ መሻት፣ መስማማት፣ መዋደድ |
| ረቂቅ | ብልህ፣ አስተዋይ ሆነ፣ ተጠበበ |
| አዘኔታ፣ | ርህራሄ፣ቸርነት፣ ደግነት፣ መራራት |
| ሳቢያ፣ | ሰበብ፣ምክንያት፣ መንስኤ |
| ስነ-ጥበብ | ስእል፣ቅርፃ ቅርፅ፣ ሙዚቃ፣ ስነ ፅሁፍ |
| ቀረበ | ተጠጋ፣ ለመድረስ ትንሽ ቀረው |
| ቀየረ | ለወጠ፣ ተካ፣ አዞረ፣ |
| የማይረባ፣ | ብልሹ ፣ የማይጠቅም |
| ባህል | ልምድ፣ ወግ |

| | |
|---|---|
| ተመቸ | ደላ፣ተስማማ፣ምቹ ሆነ |
| ተሰናኘ | ተሰራጨ፣ተስማማ፣ ተገጣጠመ ተቀኘ |
| ደረሰ፣ | አሰበ፣ አመለከተ |
| አሳየ፣ | አስረዳ፣ ጠቆመ |
| አስተናገደ: | ተቀበለ፣ አበላ፣ |
| አጠጣ፣ | ጋበዘ |
| ከመረ፡ | ቆለለ፣ ደረደረ፣ አነባበረ |
| አሳጠረ፣ | ከረከመ፣አስተካከለ፣ ቀረጠፈ |
| ውበት፡ | ቆንጆ፣ ያማረ፣ ደምግባት |
| ፈክክር፣ | ውድድር፣ ክርክር፣ ውርርድ |
| ጠመዘዘ፣ | ጨመቀ፣አንጠፈጠፈ |
| ፀጋ፡ | ሀብት፣ ስጦታ፣ ረድኤት |
| ጨረሰ፣ | ፈፀመ፣ አጠናቀቀ፣ ሰራ፣ አደረገ |

# ዋቢ ፅሁፍች


ቅድሰት ማርያም ዩኒቨርሲቲ (1995) ስነ ቃል፡፡ አዲስ አበባ፣ ያልታተመ፡፡

በላይነሽ የሻው እና ቢረሳው ታደሰ (2010) አማርኛ 3ኛና 4ኛ ክፍል፡፡ አዲስ አበባ፣ አስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ባህል ወ ቱሪዝም (2008) አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ቅፅ 7፣ ቁጥር 12፣ 7-8፡፡

ባየ ይማም (2004) አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው፡፡ አዲስ አበባ፣ አልፋ ፕሪንተር፡፡

አላምረው ገብረ ማርያም (2002) አማርኛ መማርያ መፅሀፍ 1-4ኛ ክፍል፡፡ አዲስ አበባ፣ አልፋ ማተሚያ ቤት፡፡

አስምረት ብስራት (2013) የዛሬ አበባዎች የነገ ፍሬዎች፡፡ አዲስ ዘመን ጋዜጣ

አብርሃም እንደሻው (ዓ/ም ያልተጠቀሰ) ኢትዮጲስ ቁጥር 2

አዲስ ዘመን (2013) የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት፡፡ ከዌብሳይት ላይ የተወሰደ፡፡

ከበደ ሚካኤል (1999) ታሪክና ምሳሌ ፡፡1ኛ መፅሃፍ፣አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ውዲላት ገዳሙ (2010) ብድሯን ያልከፈለች ወፍ፡፡ አጠቃላይ አማርኛ አጋዥ ከ1-4ኛ ክፍል ኤች ኬ አሳታሚ

ፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣንና ትምህርት ሚኒስቴር (2011) የትምህርት ቤቶች የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ክበባት አደረጃጀትና አሰራር፡፡ ንቁ በርታ ማተሚያ ቤት፡፡

ዲንኤል ወርቁ (2011) የተማሩት እህትማማቾች፡፡ አዲስ አበባ፣ USAID- READ II PROJECT::

ዲንኤል ወርቁ (2011) የዛፎች ጠላት ማን ነው፡፡ አዲስ አበባ፡፡ USAID- READ II PROJECT

USAID (2019) የሀና ጊዜ አጠቃቀም፡፡ አዲስ አበባ፣ READ II PROJECT::

USAID (2019) የመጓጓዣ አይነቶች ፡፡ አዲስ አበባ፣ READ II PROJECT::

USAID (2019) የቅድስት የውሎ ዘገባ፡፡ አዲስ አበባ፣ READ II PROJECT

| ከ 1 እስከ 10 | |
|---|---|
| የአማርኛ ቁጥሮች | የአረብኛ ቁጥሮች |
| ፩ | 1 |
| ፪ | 2 |
| ፫ | 3 |
| ፬ | 4 |
| ፭ | 5 |
| ፮ | 6 |
| ፯ | 7 |
| ፰ | 8 |
| ፱ | 9 |
| ፲ | 10 |

| ከ11 እስከ 19 | |
|---|---|
| የአማርኛ ቁጥሮች | የአረብኛ ቁጥሮች |
| ፲፩ | 11 |
| ፲፪ | 12 |
| ፲፫ | 13 |
| ፲፬ | 14 |
| ፲፭ | 15 |
| ፲፮ | 16 |
| ፲፯ | 17 |
| ፲፰ | 18 |
| ፲፱ | 19 |

| ከ 20 እስከ 100 | |
|---|---|
| የአማርኛ ቁጥሮች | የአረብኛ ቁጥሮች |
| ፳ | 20 |
| ፴ | 30 |
| ፵ | 40 |
| ፶ | 50 |
| ፷ | 60 |
| ፸ | 70 |
| ፹ | 80 |
| ፺ | 90 |
| ፻ | 100 |
| | |

| ከ 200 እስከ 1000 | |
|---|---|
| የአማርኛ ቁጥሮች | የአረብኛ ቁጥሮች |
| ፪፻ | 200 |
| ፫፻ | 300 |
| ፬፻ | 400 |
| ፭፻ | 500 |
| ፮፻ | 600 |
| ፯፻ | 700 |
| ፰፻ | 800 |
| ፱፻ | 900 |
| ፲፻ | 1000 |

| ከ 2000 እስከ 10000 | |
|---|---|
| የአማርኛ ቁጥሮች | የአረብኛ ቁጥሮች |
| ፳፻ | 2000 |
| ፴፻ | 3000 |
| ፵፻ | 4000 |
| ፶፻ | 5000 |
| ፷፻ | 6000 |
| ፸፻ | 7000 |
| ፹፻ | 8000 |
| ፺፻ | 9000 |
| ፻፻ | 10000 |
| | |

| ግዕዝ | ካዕብ | ሣልስ | ራብዕ | ሐምስ | ሣድስ | ሣብዕ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ |
| ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |
| መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ |
| ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ |
| ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ |
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ |
| ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቼ | ች | ቾ |
| ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ |
| ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኜ | ኝ | ኞ |
| አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ |
| ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ኼ | ኽ | ኾ |
| ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ |
| ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ |
| ዠ | ዡ | ዢ | ዣ | ዤ | ዥ | ዦ |
| የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ |
| ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ |
| ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጄ | ጅ | ጆ |
| ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ |
| ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ |
| ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጬ | ጭ | ጮ |
| ጰ | ጱ | ጲ | ጳ | ጴ | ጵ | ጶ |
| ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ |
| ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ |
| ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ |
| ቨ | ቩ | ቪ | ቫ | ቬ | ቭ | ቮ |